Scanned by CamScanner

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቤተ መጻሕፍት
A. A. UNIVERSITY
LIBRARIES

መብቱ የደራሲው ነው ።



## መግቢያ

ምናልባት «ከበልግ» ለጥቆ ፡ ከቴአትር ድርሰቶቼ መሃከል ሰፊ የሕዝብና የጋዜጣ ሐተታ ያስከተለ «የከርሞ ሰው» ይሆናል ። አስቀድሞ ድርሰቱን በሃሳቤ ስነድፍ ፡ የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን ቴአትር የገንዘብ ፡ የቴክኒክና ሌላም ልዩ ልዩ ቀዋሚ ችግርና መሰናክል በቅርብ በመመልከት ፡ ብጥቂት ተዋንያን ተመጥኜ ፡ በአነስተኛ የማያራቅ ወጪ ተቆጥቤ ፡ ሙሉ ዝግጅት ለማቅረብ የምችልበትን ዘዴ በሥራ ለመፈተን ነበር ። ይህ ሁናቴ ፡ ለሙሉ ዝግጅት ጥናት የሚመደቡትን ጥቂት ተዋንያን ፡ ጠቅላላውን የትርኢት ጊዜ ባለማሰልቸት ነቅተው ማዝለቅና መዝለቅ ስለሚጠይቅባቸው ፡ ተሰጥዎአቸውንም ይፈትናል ማለት ነው ።

«የከርሞ ሰውን» ድርሰት በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ብጨርሰውም ፡ ፍሬ-ሃሳቡን በሕሊናዬ ሳመላልስ ፡ የቱን ያህል ጊዜ እንደወሰድኩ ጠንቅቄ አላስታውስም ። የቴአትሩ አደራረስ ፡ ዘመናዊ ተብለው ከሚታወቁት ዓይነቶች ፡ በተለይ "Theatre of Cruelty" ማለት ፡ መፈስን - ቢያስጨንቅ be ruled. That was what happened to ይመደባል ። A wedge was driven into his soul . . . all

የቴአትሩ...ers on it ... he was made to feel small

አስታ...ity. His aspiration and integrity were destroyed permanently. He thought he must live for others and still survive. He tried the impossible. When a man gives up his self-

«ባሁኑ በመሸጋገሪያ ጊዜ ያለውን የእምነትና የስነ-ምግባር ዝብርቅርነት ደህና አድርገው አቅርበውታል ።»

አዲስ ዘመን - ፳፫ኛ ዓመት ቁ. ፻፺ ።

«የተውኔቱ ይዞታና መልእክት ባለንበት ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን ጠቅላላ ችግር በሦስት መስተዋንያን አማካኝነት ብቻ ለማስረዳት የሚሞክር ነው ።»

አዲስ ዘመን - ፳፫ኛ ዓመት ቁ. ፻፺፬ ።

« . . . . ይኸውም ፡ . . . . . የአሁን አኗኗራችንን ግልጥ አድርጐ የሚያሳይ ቴአትር . . . . .ነው ።»

የኢትዮጵያ ድምፅ - ፲ኛ ዓመት ቁ. ፪፻፴፯ ።

«ግብርና . . . . እንደጥንቱ . . . . .ለዕለት ጉርስ የምትበቃ አንዲት ማሳ መሬት እየጫሩ ፡ ለዘለዓለም ከሞፈር ቀንበር ጋር መታገል አይደለም ። . . . .ዛሬ ጊዜ ተአምርን የሚያስገኝ የሰው ሥራ ነው ። . . . . ገበሬውን ዘመናዊው ብልጭልጭ እየሳበው ወደ ከተማ ሲጐርፍ ፡ የተማረው ደግሞ ከተማውን የሙጥኝ ይዞ አለቅም ብሏል ። . . . . .

[illegible] ሹራ [illegible] ተቀደደ

[illegible]ኛ ዓመት ቁ. ፪፻

[illegible]ዩቶ ችግራ



እያባከነ የሚያወራው ? . . . . . የውስጥን ስሜት እንደ ቅዠት ያባክናል ። ትካዜን ፡ ትዝታን ፡ ሐዘንን ያጫፍራል ። . . .» አዲስ ዘመን - ፳፫ኛ ዓመት ቁ. ፪፻፩

« . . .ካለፈው መማራችን ያሁኑን አሳምረን እንድን ይዘው ይረዳናል ። ያሁኑ ትግላችን ደግሞ ለመጪው መሠረት ይሆናል ። . . . . መታሰቢያነታቸው የማይረሳ ፡ ለተተኪው ትውልድ ምሳሌ ሆነው የሚተላለፉ (ቴአትሮች) ይበልጥ ተወዳጅነት አላቸው ። . . . . የሚጠቅመንን ለመምረጥ መቻል የእኛ ፋንታ ነው ። . . .»

የኢትዮጵያ ድምፅ - ርዕስ አንቀጽ - ፲ኛ ዓመት ቁ. ፪፻፵፱

«የከርሞ ሰው የኀዘን ድባብ የተደበበበት ቴያትር ነው ። መድረኩ የችግር ወጀቦ ያላጋው ይመስላል ፡ አነጋገሩ ልብ ይነካል ። . . . . አየሁት ፤ አደነቅሁት ፤ ተቸሁት ። ቢያምረኝ ቢጥመኝ ነው ። . . .»

አዲስ ዘመን - ፳፫ኛ ዓመት ቁ. ፪፻፲፪

«Since the soul is that which can't be ruled, it must be broken in order to be ruled. That was what happened to «Yekermo Sew.» A wedge was driven into his soul . . . all got their fingers on it ... he was made to feel small . . . feel guilty. His aspiration and integrity were destroyed permanently. He thought he must live for others and still survive. He tried the impossible. When a man gives up his self-

respect he is finished. He will obey any situation, . . . . any man for that matter. . . . . he can't trust himself any more, he feels uncertain, unclean. That was what happened to «Yekermo Sew.» THE ETHIOPIAN HERALD - Vol. VI - No. 211.

«...... one of the phenomenal problems plaguing the developing societies to day is the controversy over conflicting values. When people belonging to different generations find themselves living together conflicting attitudes are bound to arise ......... as result of this tug of war, the question of national identity remains at stake ......... The theme is not something new but the author has given it a new flarour through excellent gialogue. . . . . In «Yekermo Sew» while . . . . . . . . . derides the uncompromising attitude of the old and the futility of the young..... at the same time underlines that modern Ethiopianism is being challenged by foreign cultures.» MENEN - VOL. XI - No. 11.

ያንዳች የኪነ ጥበብ አሰካክ ፡ እንደሚገባው ሆኖ ያላገኘሁት ሲመስለኝ ነፍሴ ትቆጣለች ይላል በርናርድ ሾው። ስለዚህ እያንዳንዱ ተመልካች ፡ የትርኢቱ ጠቅላላ ሁናቴ በየነፍሱ ላይ ባሳደረበት ውጤት መጠንና ደረጃ ፡ ነፍሱ ትቆጣለች ፡ ትረካለች ፡ ታደንቃለች ፡ ወይም ታወግዛለች። ጠቅላላው ትርኢት በተመልካቹ ሕዝብ መንፈስ የተቀራረበ ወይም የተመሳሰለ አስተያየት ፈጥሮ እንደሆነ የፍሬ ሃሳቡን ዓላማ አስገኝቷል ሊባል ይቻላል ። የኪነ - ጥበባት



ትችት መነሻ ሁሉ ይኸ ነው ፡ ፍሬውም ይኸው ነው ፡ ሊሆን ይገባል ፡ የተረፈ ሐተታ ግን ያው ትርፍ ሐኬት ነው ።

ቶልስቶይ ፡ የሥነ ጽሑፍ ሁሉ ዓላማ ለሰው ልጅ በጎ ካልሆነ ፡ ሥነ - ጽሑፍ ሊሰኝ አይገባም ይላል ። ምናልባት ዛሬ በኪነ - ጥበባት ስም የተነሱት ብዙ ተቃራኒዎቹም ፡ ክርክራቸው ለብሩኅ ኅሊና ግምት እስካላጠገበ ድረስ ፡ ተቃውሞአቸው ሥር አልሰደደምና የሱን አስተያየት ገና አላሸነፉትም ።

«የከርሞ ሰውን» ቴአትር አምና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ባዘጋጀሁት ጊዜ ፡ የሦስቱን ክፍል ባሕርይ (ካራክተርስ) በበጎ ፍቃድ የተካፈሉትን ተዋንያን ፡ ተስፋዬ ሣህሉን እንደሞገስ ፡ አውላቸው ደጀኔን እንደአብዬ ዘርፉ ፡ ጌታቸው ደባልቄን እንደተኮላ ፡ ለአንባቢያን ላስታውስ እወዳለሁ ።

ጸ . ገ . መ .

## ገቢር አንድ

### ሀ

ጐላ ሠፈርም አዲሱ አዲሳባ እምብርት ውስጥ ነው ። ሞገስ የውሀና የመብራት ችሎ በአሥራ ሦስት ብር የተከራያት በጋዜጣ ወረቀትና በሳሙና ሳጥን የተለደበችና የተጠጋገነች ማዕድ ቤት የምታህለው አንድ ክፍል ጐጆ «ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል» ናት ። ባለቤቱ ባሻ ተሊሳ ከመገዛ ጓሮአቸው ሽፍሻ -ፊ ተቀጥላ አድርገው የተከሏት ለመኖርያ ትሆናለች ብለው ሳይሆን የቶቸገረ አንገቱን ሲያስገባ ለሳቸውም አሥራ ሦስት ብር ያስገባ እንደሁ ብለው ነው ። ገንዘቡ ለሳምባ ነቀርሳ ሕመማቸው ህክምና እጅግ ያስፈልጋቸዋል ።

ሞገስ ተገባባት ሦስተኛው ዓመት ባለፈው ወር ጀመረ ። የመዝገብ ቤት ጸሐፊ ሆኖ በ[illegible]ሳ አምስት ብር [illegible] ቀ[illegible] አሥራ አንድ ዓመት ሆ[illegible]ው ። በዚች በአሥራ አንድ ዓመት ውስጥ ከትጋት ጭልቅ ጥንቃቄንና አንገት ማቀርቀርን አውቋል ። ሠላሳ ሦስት ዓመቱ ነው ። የዛሬ ሁለት ዓመት ነው ከሚስቱ የተለያየው ። ነርቭ በሚሉት የደም ሥር ሁከት ምክንያት አእምሮው ተነክቶ አማኑኤል ሆስፒታል ሁለት ወር በተኛበት ሰሞን አራስ ልጅዋ በድንጋጤ እንዳይሞትባት በማለት ሞገስ ከሆስፒታል ሳይመለስ ይዛው ኮበለለች ይላሉ ። ግን እሱን ለዚህ በሽታ ያበቃው ብስጭት አማርሮአት ስለነበረ የመገላገያ ምክንያትና ጊዜ እስኪያመቻት ትጠባበቅ ነበርና በዚያን ሰሞን ቶሎ ሾልካ

ነው እንጂ ወትሮም በቅቶአታል የሚል ወሬም አለ ። መን ደሩ ለአውራ መንገድ ቅርብ በመሆኑ የመኪናዎች ሞተር ባለማቋረጥ ይሰማል ።

የሞገስ ታናሽ ወንድም ተኮላም አብሮት ይኖራል ። ተኮላ በአካል ብቻ ሳይሆን በአእምሮም የጠጠረ የሃያ ሦ ስት ዓመት ጉርባ ነው ። አጐታቸው አብዬ ዘርፉ የዘመድ አዝማድ መርዶ ይዞ ከመጣ አሥር ቀን ሆነው ። የአባታ ቸውንም የአንድ ጋሻ መሬት ውክልና ለልጆቹ መልሶ ለማ ስረከብ ወስኖአል ። አቶ ዘርፉ በስድሳ ሰባተኛ ዘመኑ የአን ጀት መቁሰል በሽታ ካደረበት ሰንብቶአል ።

ቀኑ ቀዳሜ ነው ። መጋረጃው ሲከፈት ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተሩብ ነው ። ሞገስ ካልጋው ተነስቶ ከበረንዳ ጥግ የሚገኘው ጠርሙስ ውሀ ፊቱን ይታጠባል ። አቶ ዘርፉ ከበስተግራ በሚገኘው የእንጨት አልጋ ላይ ተኝቷል ። ከራስጌ አንድ ጨብ ከነአሮጌ አሮጌ ተሰቅላለች ።

የቤቱ መግቢያ በር ከበስተግራ ነው ። የበስተጀርባው ግድግዳ ከባለቤቱ ጓሮ የተቀጠለ በመሆኑ እንደበስተቀ ረው የሳሙና ሳጥን ዛኒጋባ ሳይሆን የጭቃ ማገር ነው ። የሞገስ የቦንዳ ብረት አልጋ ከዚሁ ግድግዳ ተደግፎ ቆ ሟል ። ከዚሁ አልጋ ግርጌ ከፍ ብሎ የተሸነቈረው ቀዳዳ መጨቅጨቂት በመሰለ እራፊ ተወትፎአል ። ውታፉ ሲከ ፈት ከባሻ ተሊላ ቤት ውስጥ ጢስ ወዲህ ይገባል ። ከመግ ቢያው በር ፊት ለፊት ካለው ጠረጴዛ ላይ ግማሽ የሲሙ...



ዳቦ ፤ ሁለት የዲቴክቲቭ ልብ ወለድ የእንግሊዝኛ መጻሕ ፍት ፤ አንድ ፔርሙዝ ምድጃና ክብሪት ፤ ከሥሩም ጨርቁ የተበጣጠቀ ሶፋና አንድ የእንጨት ወምበር ባዶ ትሪይ የተቀመጠበት ይታያል ። ከሶፋው ራስጌ ክራር ተሰቅሎ አል ። ተኮላ ጣቱን በደፉ ቀዳዳ አሾልኰ የበሩን መወርወ ርያ ከፍቶ ሲገባ ሞገስ ተነስቶ በማየት ቆም ይልና ወዲያው አንገቱን እንደ አባያ በሬ ቀልሶ ያልፍና ትሬውን መሬት አስቀምጦ ወምበሩ ላይ ተንፈራጥጦ ይወዘፋል ። ሞገስ እንዳላየ ዝም ይላል ።

ተኮላ

(ከአጭር ጸጥታ በኋላ የእግሩን ጫማ አገላብጦ እያስተዋለ-) እንዳን ሰባተኛ ክፍል አንድም ጫማ የሌለው ተማሪ የለ ። ...... የኔ አ ዶቹማ ሦስት አራት ቅያሬ ነው ያላቸው ። ንድ ቱም ሶሏ በጠጠር ከተሸነቆረች ሰባት ቀን አለፋት ። (ቀኙን እግሩን ጫማ አውልቆ ሌባ ጣቱን በሶሉ ቀዳዳ ውስጥ አሾልኮ) ይኸውልህ ። እንኳን ከእንቅፋት ልታድነኝ የእግሬን ጣት እያሾለከች እንቅፋት ሆናኛለች ። በመከላከል ፈንታ ታደናቅፈኛለች ። (ጫማውን መልሶ የጠላ ኳር ... እያየ-) ጊዜውን እንም የእግር አውራ ጣት በ... ስል ከተነጠ ሸንቁር ጫማ ያስነውራል ። እኛ ክፍል አንድም ጫማ የሌለው ተማሪ የለ ።

Scanned by CamScanner

ሞገስ

(ፀጉሩን በፎጣ እያበሰ በቸልተኝነት) ለዚህ ነው ሰባተኛ ክፍል ሁለት ዓመት ደግመህ በሦስተኛው አስተማሪህን ደብድበህ የወጣኸው? (ረዥም ፀጥታ ።) የሞገስ ሸሚዝ መናኛ ናይሎን ነው ። እንገትጌውም እንደ ክራባቱ ጭምድድ ብሎአል ። ቡላ ኮቱ አሮጌ የመሸታ ሱፍ ሲሆን ናይሎን ሱሪው እጉልበቱ ላይ ተኮፍሶ ኳስ ያዘለ መስሎአል ።)

ተኮላ

መቸም ተጓደኞቼ ተለይቼ እኔ ብቻ አለጫማ ልዘልቅ አልችልም ። በክፍላችን ጫማ የሌለው ተማሪ አንድም . . . .

ሞገስ

(ያቋርጠውና ይልጐመጐማል) እኔን ያሰጋኝ ሸንቁር የጫማህ ሳይሆን የአእምሮ ልቦናህ ነው ። (ረዥም ፀጥታ ።)

ተኮላ

(ጣራ ጣራ እያስተዋለ እንደዋዛ) በትምህርት ቤት ውስጥ ጫማ የሌላቸውን ወንዶች ልጃገረዶቹ ምን እንደሚሉዋቸው ታውቃለህ?

ሞገስ

(አልጋውን ማነጣጠፍ እየጀመረ) ለማወቅ አልፈልግም ፤



ተከላ

(ጉፍንን እንደማለት ብሎ -) እኔ በበኩሌ . . . . እኔ በበኩሌ .

ሞገስ

(ያቋርጠዋል) እኔ በበኩሌ ብለህ ነገር አትጀምር ።

ተከላ

ለምን ?

ሞገስ

አትጀምር ።

ተከላ

ለምን ?

ሞገስ

እኔ በበኩሌ ብሎ የሚጀመር ነገር ሁሉ የንፉግ ትችት ይመስለኛል ።

ተከላ

የንፉግ ትችት ምንድነው ? . . . . ምንድነው ?. . . . . . . .

ሞገስ

(ሲገላምጠው ተከላም አተኩሮ ይመለከተዋል ። ሞገስ በመጠኑ ኮስተር ብሎ) እሱን ተወውና ዛሬ ደሞ የት አድረህ እንደመጣህ ንገረኝ ። (ረዥም ፀጥታ ።)



ተከላ

(አብዬ ዘርፉ ወደተኛበት አልጋ በደንደሳም ትከሻው እያመለከተ ) ይኸ እያለ እምን ላይ ልደር ብለህ ነው ? መኝታዬን እንደሁ በቁም አስወርሰኸኛል ።

ሞገስ

ድሮ ሶፋው ላይ አልነበር አርፈህ እምትተኛው ?

ተከላ

ሶፋው ይጠበኛል ። እግሬን እንኳን አያዘረጋኝም ። (ይጋደምበትና -) እየው ። ኩርምትምት ነው እሚያደርገኝ ። በዚህ ላይ ያገጠጠ ሽቦው ጀርባዬን ሐዲድ አስመስሎታል ። አያሳርፍ ፤ አያገላብጥ ፤ እስርስር ያለ ወጥመድ ። (እግሮቹን እንፈራጥጦ ውዝፍ ይልበታል ።)

ሞገስ

(አሁንም በመጠኑ ኮስተር ብሎ) የት አድረህ መጣህ እኮ ነው ያልኩት !

(አጭር ፀጥታ ።)

ተከላ

(ትንሽ እንደመልጐምጐም ካለ በኋላ በፍጥነት ያነበንባል) አንተ እሱን ለምን ሂድ አትለውም ? ለምን ሂድ መኝታው

Scanned by CamScanner

ን ልቀቅለት አትለውም ? መርዶውን እንደሁ አርድቶን እርማችንን አውጥተናል ። በተረፈ ምን እዚህ ይዘፈዝፈ ዋል ? ያያታችሁ እህት ልጅ ሞተች አለን ፡ አለቀስን ፤ የ ሚስቴ አጐት በተስቦ ሞተ አለን ፡ አለቀስን ፤ አሁንስ እሱ እራሱ እስኪሞትብን ነው እሚጠበቅ ? አይሄድም ? አን ጀቴ ቆስሎአል ይላል ፤ ታድያን እኛ የአንጀት ወጌሾች አደ ለን ። ገንዘብ የለኝም በለው ። ሂድ በለው ። አጐታችሁ ነኝ አለን ፡ እኛም ዓሚን አብዬ ዘርፉ ብለን ተቀበልነው ። አ ሥር ቀን ሙሉ አብዬ አብዬ አልነው ። አይበቃውም ? አይ ሄድም ? ያባታችሁን ርስት ደን ዋጠው ይላል ። የለም ጠፍ የነበረው ጋሻ መሬት ጠፍ ሆነላችሁ ይላል ። ሂዶ አያለማ ውም ? አፈር መግፋቱን እንደሁ እሱ ነው እሚያውቅበት። ገንዘብ የለኝም በለው ። በዚህ ላይ የቤት ኪራይ ፤ የአልጋ ኪራይ ፡ የመብራት ፡ የውሀ ፡ ምኑ ቅጡ ። ሂድ በለው ። . .

ሞገስ

(በትዕዝብት -) ይኸ ሁሉ እኮ የጥያቄዬ መልስ አደለም ተከላ ።

ተከላ

(እንዳልሰማ ይቀጥላል) የገጠር ሰው ሁሉ አባታችሁን መስላልህ ይለኛል ይላል ። ታድያ ምን ይጠበስ ? አባባ የመሰለ እንደሁ ምን እናድርገው ? እኔ እንደሁ አባባን



ውቀው ነው የሞተ ። እኔ ተረግገፎ ነው አሉ ማይጨው የም ትሉት ሄዶ የቀረው ። እናቴንም አላውቃት ፡ ሳታሳድገኝ ነው የሞተች ። ዓሚን ። (ከበስተጀርባ የአቶ ተሊላ ሳል ይ ሰማል -) ይኸ ደሞ የቤቱ ኪራይ ሲደርስ ብቻ ነው መሰለኝ የነቀርሳው ሳል የሚቀሰቀስ ። ያለፈውም ወር አልተከፈለ፤ ካምስተኛ ወረዳ መጥሪያ አስመጣብሃለሁ ሲል ነበር ፤ አሁ ንም አልከፈልከውም ? (ሞገስ የአልጋውን ደምብ ደገፍ ብሎ በትዕዝብት ያስተውለዋል -) ይኸማ የአፈርን ጣዕም የሚያውቅ ገበሬ አባታችሁ ብቻ ነበር ይላል ። አገር የቀ ናበት አራሽ ነበር ይላል ። ስለዚህ ምን ይሁን ? እኮ ምን ይፈጠር ነው እሚል ? የመኪናው ጩኸት ያቃዣል ይ ላል ፤ ትቶት አይሄደውም ! ቁሽቱ ቆሰለ ይላል ፡ ቅዱስ ጳ ውሎስ ሆስፒታል ተመርምሬ ተመላልሰህ ታከም ጨጓራ ህ ተልጧል አሉኝ ይላል ፤ አሥር ቀን ሙሉ ተመላለሰ ፤ አይ ሻለውም ? አባታችሁ የማይጨው ጀግና ነበር ይላል ፤ እው ነተኛ ክርስቲያን ነበር ይላል ፡ ብርቱ ገበሬ ነበር ይላል ፡ አባታችሁን ምሰሉት ይላል ፡ አለመምሰላችንን በምን አ የው ? በምን አየው !

ሞገስ

(ትዕግሥቱ አልቆ ድምጹ የንዴት ነው -) ያደርከበትን ንገ ረኝ እኮ ነው እምልህ !

Scanned by CamScanner

ተኮላ

(ብስጭቱ ከድንጋጤው ይጠናል ፡ እልህ ይዞት ፡ ግራ ገብቶት እንደመቁነጥነጥ ይላል ፡ ፈንገጥ ብሎ ሊወጣ ይቃጣና በራፉ ላይ ሲደርስ መለስ ብሎ በሚሟማው ተረከዝ ወለሉን እንደቁጡ ውሻ እየጫረ ሲቃ ባነቀው ድምጽ -)

እ . . . . . . እሚዋጥ መከላከያ አለህ ?

ሞገስ

ምን እሚዋጥ ?

ተኮላ

ፔኒሲሊን ።

ሞገስ

ፔ . . ፔኒሲሊን ?

ተኮላ

(እምባ እየተናነቀው በጩኸት) አዎን ፔኒሲሊን ! ፊኛዬን ይወጋኛል ። . . . የት አደርክ አላልከኝም ? የት ያደርኩ ይመስልሃል ! ( ከአጭር ፀጥታ በኋላ ሞገስ በድንጋጤ ኪሶቹን ሁሉ ይዳብሳል - ከውስጠኛው የደረት ኪሱ ውስጥ የፕላስቲክ ቦርሳውን ያወጣል ፡ ሲከፍተው ባዶውን ነው ፤ ሲበረብረው አንድ ፎቶግራፍ ይወድቃል ። ቦርሳውን መልሶ ከሱሪው ምስጢር ኪስ ውስጥ አንድ የተጠቀለለች ብር ያገኛል ፡ በኝኮላ ለተኮላ ይሰጠዋል ። ተኮላ ብሯን ቀበል ብሎ እ[illegible]ን ኪሱ ውስጥ ከነእጁ እምቅ ያደርጋትና ውልቅ ይላል ፡ ሞገስ በትካዜ ይዋጣል ።) . . . . . . .



ሞገስ

(አልጋው ጫፍ ላይ ደገፍ ይልና አንገቱን አቀርቅሮ በዝግታ ያነበንባል ፡-) ልጅ ሆኜ አባዬ ከሞተ በኋላ እማማ ስትገስፀኝ ድምጿን ዘለግ አርጋ "ሞገስ" ትለኝ ነበረ ። ሞ-ገስ ፡ እንቅፋት አፍጥጦ ሲመጣብህ ዝቅ ብለህ ሹለከው እንጂ በቁም አትጋተረው ትለኛለች ። የወንድሜን ልቦና የተዋሀደው ተግሳፅ ግን የምክር ዓይነት ሳይሆን የዘለፋ ዓይነት ነው ። የውይይት ሳይሆን የድፍረት ነው ። ተኮላ የስሜቱን ጽናት የሚያነጻጽረውና የሚያመሳስለው በአስተያየትና በይሉኝታ ሚዛን ሳይሆን በመኪና ኳኳታ ፡ በጋሪ ፈረስ ኮቴና በፖሊስ ፊሽካ ፉጨት ነው ። (ከተቀመጠበት ቀና ብሎ ጣራውን እያስተዋለ ፡-) ለዚህ ይሆን በመግባባት ሳይሆን በመጋጨት የሚያምነው ? በእግዚአብሔር ጸጋ ሳይሆን በፔኒሲሊን የሚያምነው ? "ተው ተኮላ" ሲሉት የመከሩት ቀርቶ የገሠሙት ይመስል ኩፍ ይላል ። ሰብዓዊ ፍጡርነቱ እንኳ ትዝ ሲለው ዝግንን ብሽቅጥ ይላል ። የሳት እራት ብርሃን ፍለጋ ወላፈን ውስጥ እንደምትከስት የወንድሜም ቀልብ በዓይን አዋጅ ተሰልቦ ፡ በብልጭልጭ ተታሎ ይባክናል ። (ከበስተጀርባው ቤት የአቶ ተሊላ ሳል ይሰማዋል ። አጭር ጸጥታ ። ካልጋው ጫፍ ተነስቶ ወደ መሀል መድረክ ወረድ ይላል ፡-) ትሁኔ ትታኝ ከመኮብለሏ በፊት ፡ ሚስቴ ከመሄድዋ በፊት ፡ ው- ወፈፌ ነው ብላ

ጥላኝ ከመሄድዋ በፊት . . ለልጃችንና ለኛ አንገት ማስገቢያ የምትሆን ዛኒጋባ ብጤ ሳልቀልስ ብዬ እታትር ነበርኩ . . . . . አሁንም ሀሞቴ ፈሰሰ እንጂ ተስፋ አልቆረጥኩም ። . . . . . . . . ያሁን ጥረቴ ዛኒጋባ ለመቀለስ ሳይሆን ተስፋ ላለመቁረጥ ነው ። . . . . አዎን ፡ ዓላማዬ ሁሉ ለመደርጀት ሳይሆን ተስፋ ላለመቁረጥ ብቻ ሆኖ ቀርቷል ። ሀሞቴ እንኳ ቢፈስ የእማዬ ተግሳፅ ትዝ እያለኝ "ተውሞ-ገስ" እለኛለሁ ። አዎን ፡ እኔው እራሴን እየታዘብኩት እየገሰፅኩት ነገርኩት ። ፀጥ እንዲል ነገርኩት ! (መረር ባለ አንደበት -) ተኮላ ግን «ሴትና ይሉኝታ ያከበራትን ነው እምታጠቃ ፡ ዓለም በገላመጠችህ ቁጥር በልቦናህ የሌለብህን ጉድፍ በጥርጣሬ እውስጥህ በመፈለግ ነው እንዳይሆን አርጋ የምትጫወትብህ ፡ መፋጠጥና መጋተር ብቻ ነው እሚያዋጣ" ይላል ። እኔ ግን ለኔነቴ ነገርኩት ፤ "ተው ሞገስ" አልኩት ፡ እንዲቀል ገሰፅኩት ። ፀጥ እንዲል ፡ ኮስተር እንዲል ፡ ለጥ እንዲል ፡ ቀጥ እንዲል ነገርኩት ። ሀሞትህም ቢፈስ ተስፋ አትቁረጥ አልኩት ። "ሞገስ" አልኩት ። (የተሊላ ሳል ሜን ብሎ ይሰማል ። የሞገስ አንደበት ለዘብ ብሎ ይቀጥላል ።-) የልጃችን ስም ይጥና ይሁን ብላት "ድጋፌ" "መኩሪያዬ" "ክንዴ" ካ





ልሆነ ብላ አሻፈረኝ አለቺኝ ። ኮከቡን አስቆጥሬ "ይጥና" የሚል ስም አልሠምር ብሏል አለቺኝ ። ድጋፌ ከመ ባሉ በፊት ይጥና መባሉ አይሻልም ብላት ፡ -ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ - ፡ አሌ አለች ። ወ -ወፊፌ ነህ ብለው አማኑኤል ያሳደሩን ዕለት ሌሊቱን ልጃችንን ይዛ ኮበለለች ። ሐኪሙ ግን በሽታህ የ-ነርቭ ነው አለኝ ። የደም ሥርህ መ-መታወክ መ-መቆጣት መ-መታወክ ነው አለኝ ። ብ-ብቻ በማግሥቱ ስመለስ ልጇና ትሁኔ ቤት አልነበሩም ። . . . እ-እንዳላስፈልጋት ፡ አማላጅ እንዳልከባት ደብር ደውላ በገበዝ አስገዘተችኝ ። ጐ-ጐቤት ጀርባውን አዞረብኝ ፡ ሕፃናት ጣቶቻቸውን አሾሉብኝ ፡ ጓ-ጓደኞቼ ቡ-በሹክሹክታ አንደበታቸውን ቀለሱብኝ ፤ እኔም ጓዳ ውስጥ ተወሽቄ ፡ ም-ምድሯን ቢጥጩ ፤ ግድግዳውን ታቅፌ ፡ ድምጼን ቀ -ቀብሬ ተ-ተንሰቀሰቅኩ ። ያ-ያለተኮላ አይዞህ ያለኝ አልነበረም ። እ-እግዚአብሔር እንኳ ጀርባውን ያዞረብኝ መሰለኝ ። የ-የተጋለጥኩ መሰለኝ ። ተ-ተኮላ ግን ፡ "አይዞህ ጋሼ" አለኝ ። . . . ይሁንና ከዚያች ዕለት ጀምሮ ከኔ ልብ ይልቅ የሱ በጭካኔ ተነደፈ ፡ ከኔ ይልቅ እሱ ሰው ፈራ ፡ ሸሸ ። ሰው አውሬ ነው ብሎ ራሱ አውሬ ሆነ ። ተ-ተኮላ . . . . . (ከቅራቢያው መሥሪያ ቤት የምስት ሰዓት የኤሌትሪክ መለከት ሲያስተጋባ ይሰማል ፡ ሰዓቱን ሲያይት ቂማለች ፡ የተጨማደደች ሸሚዙን እያስተካከለ ፡ አሊጋው እራስጌ አተዘቀለው መስተዋት ውስጥ ፊቱን መልከት ይልና ወደ በሩ ተፍ ብሎ ይ ሎ ። ዘርፉ ወደተኛበት አልጋ መለስ ይልና የፊቱን ከ ብ

ንብ ገለጥ አድርጎ -) አብዬ ፡ አብዬ ፡ ተነስ ተነስ እረፍ ደል ። ቁርስ ብጤ ጠረጴዛው ላይ አለልህ ። ተነስ እረፍ ደል ። (በችኮላ ይወጣል ። ዘርፉ እያቃሰተ ፡ እያዛጋና እየ ተንጠራራ ሲነሳ ከጓሮ የመኪና ሞተሮችና የተሊላ ሳል ጐላ ብሎ ይሰማል ።)

ዘርፉ

(አብዬ ዘርፉ ስናፊል ስራውን ከተንተራሰበት ራስጌ አንስቶ በብርድ ልብሱ ውስጥ እየታጠቀ በዘልማድ ጸሎትና በትችት እንደበት እየፈራረቀ ያነበንባል ። በጸሎት ፡-) በቀኝ አውለኝ ፤ በቀኝ አውለኝ ፤ በቀኝ አውለኝ ፤ አባዲር ፡ አባዲር ፡ ጦም አያሳድር ፡ ሰላም አውርድ ፡ በቀኝ ፡ አውል ፡ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈቅ ቅዱስ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ ( . . . ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ካዛጋ በኋላ በትችት እንደበት ፡-) አቤት ቅዣት ፡ አቤት ቅዣት ፡ ጭንቅላቴ የቅዣት ቋጥት ሆኖ መቅረቱ ነው እንዴ ? አዳር አይበለው ። የመኪናው ፤ የጥሩምባው ፡ የግርግሩ ፡ ያስረሸ ምቹው ፡ አረ ምን ቀጡ ፡ አቤት ቅዣት ፡ አቤት ቅዣት ፡ አዳር አይበለው ። (እየተንጠራራ እጅ ጠባቡን ያጠልቅና መለስ ብሎ በጸሎት እንደ በት -) አንተ ታውቃለህ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ ሰማይን አለ ባላ ፡ ምድርን አለካስማ ፡ የዘረጋህ ጌታ ፡ ተለመነን ፡ ተለ መነን ፤ የነነዌ ፤ የነበለዔ ሰብዕ ፤ የነባልአም ጌታ ተለመ ነን ፡ ተለመነን ፡ ተለመነን ፡ ኢዮብን ከዓለገነባሪ ሆድ ፡



ዳንዔልን ከአንበሳ ዋሻ ፡ አልአዛርን ከመቃብር የተፋህ ጌታ ይቅር በለን ፡ ይቅር በለን ፡ ወልደ አብ ይቅር በለን ፡ ክርስ ቶስ ይቅር በለን ፡ መድኀኔ ዓለም ይቅር በለን ፡ ይቅር በለ ን ፡ ይቅር በለን ። (መዳፎቹ ላይ እትፍ እትፍ እያለ ፊቱን እያበሰና እየተንጠራራ ካልጋ ወርዶ ጋቢውን ትከሻው ላይ ጣል አርጎ ራመድ እላለሁ ሲል እንጀቱን እንደተወጋ ያህል ሆዱን በስቃይ ጭብጥ አርጎት ኩርምት ብሎ ይቆማል ። ትንሽ ቆይቶ ትንፋሹ መለስ ሲልለት በምሬት እንደበት -) ተው ኢየሱስ ተው ! ተው የማርያም ልጅ ተው ! ተው ይኸን ቆሽት ማቁሰልክን ተው ! ተው ይኸን ጨጓራ መላጥ እሚሉ በሽታህን ተው ! ተው የማርያም ልጅ ተው ። ይኸን አንጀት ስትሮ እሚያልብ በሽታ ከየት አመጣህብኝ በል ! (በዝግታ አጐብድዶ ሞገስ የታጠበባትን ጠርሙስ ቀና አድርጎ ከሸንጧ በታች የቀረችውን ውሀ በንፍገት እያስተዋለ -) ይቺማ እንኳን ለአፏ ለማታጠብ ያ ላፊም መ ጉመጥመጫ አትበቃኝ ። አይ የከተሜ ኑሮ ! አሁን ይኸ ኑሮ ነው ? (እጆቹን ራስ ራስ አርጎ በሁለት ጣቶቹ ብቻ ዓይኖቹን አበስ አበስ ካደረገ በኋላ የቀረችውን ውሀ ሁለቴ እየተጉመጠመጠ ግድግዳው ሥር ይተፋና በንቀት እንደ በት -) አሁን ይኸ ኑሮ ነው ! (ጠርሙስዋን አስቀምጦ ቀና ሲል ሆዱን በስቃይ ደግፎ ይቀራል ። ወዲያው ትንፋሹ መለስ ሲልለት በምሬት እንደበት -) ተው የማርያም ልጅ ተው ። ተው እንደማያሆን አታርገኝ ተው ። ተው እንዲህ ፈትነህ አትያዘኝ ተው ። (እያዛጋ ፡ ትከሻው ላይ የተንጠለ

ጠለው የጋቢ ዘርፍ ወለሉን እያበሰ ፡ ዳቦዋን በወረቀት ወደ ተጠቀለለችበት ጠረጴዛ ይሄድና ያነሳታል ፡ ወዲያው ሲፈራ ሲቸር ቆርሶ ሊጐርሳት ይቃጣና እጁን መለስ አድርጐ በጥርጣሬ እንደበት -) ጾም ይሆን እንዴ ! በእንቁላል ነው አሉ የሚያቦኩት ። (የተሊላ ሳል ይሰማል ። ዘርፉ ድምፁን ከፍ አርጐ ሰላምታ ይጠይቃል ።) እንደምን አደራችሁ እዚያ ቤት ? እግዚአብሔር ይማርዎ ፡ ምሕረቱን ይላክልዎ ! (ድምፁን ለዘብ አርጐ -) አልሰሙኝም መሰለኝ ። (ዳቦውን በመኰምጀት መልከት ይልና ጨክኖ ጠረጴዛው ላይ ይወረውራታል -) ደሞ ለዚች ብዬ ገድፌ ንስሐ ልግባ ! በእንቁላል ነው አሉ የሚያቦኩት ። (እየተልጐመጐመ ወደ አልጋው ሄዶ ከፍራሹ ሥር የጥይት አሮቱ ተበጣጥቆ ያለቀ ዝናሩን እየታጠቀ -) አሁን ይኸን ኑሮ ብለው ነው ? ያን የመሰለ ያባታቸውን ርስት ሚካ ውጦት ! እነሱ በዚህ በከተማ ውስጥ ጊረኖ ተውጠው ! እውነት አሁን ይኸ እግዚአብሔር የሚወደው ኑሮ ሆኖ ነው ? (አልጋው ግርጌ የወደቀችውን ጭራ አንስቶ ቀና እያለሁ ሲል -) እምቢ አልከኝ ጌታዬ ? እምቢ አልከኝ የማርያም ልጅ ? ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በየዕለቱ መርፌ እጠቀጠቃለሁ ። በዚህ ላይ የሚዋጠው እንክብል ዓይነቱ ፡ ቀለሙ ፡ መጠኑ ፡ ብዛቱ ! ኧረ ተው የማርያም ልጅ ፡ ኧረ ተው ። (ጭራውን አልጋው ግርጌ ያስቀምጠዋል ። በርኖሱን ካልጋው ግርጌ ወደ ራስጌ ጐትቶ ከተንተራሰ በኋላ እጥፍጥፍ ብሎ ይጋደምና እንቅልፍ ሰለብ ባደረገው ድምፅ -) እሮይ !



. . . . .ምነው ጨጓራዬን ልጠህ ባትጨርሰኝ ኢየሱስ ? ምነው እንዲህ ፈትነህ ባትይዘኝ ጌታዬ ? ምነው ቈሽቴን አቁስለህ ባትገድለኝ የማርያም ልጅ ። ጀግና በጥይት ነበር የሚሞት ፤ እኔን እረስተህ ውለህ የኋላ ቀን በምን ይኸን መረጥክልኝ ? (የተሊላ ሳል ይሰማል ። በመታከት ጋደም ይላል ። ከአጭር ፀጥታ በኋላ ተኮላ በሩን ብርግድ አርጐ ይገባል ። . . . . . . .

ተኮላ

(ዘርፉ ራስጌ ይቈምና ከፍ ባለ ድምፅ -) አብዬ ዘርፉ ! አብዬ ዘርፉ ! (ዘርፉ ባንኖ ቀና ይልና በቀኝ ክንዱ ትራሱን ይመረኰዛል ።) የመርፌህ ሰዓት ደርሷል ተነስ ሂድና ታከም ።

ዘርፉ

(እንደባነነ -) እ ?

ተኮላ

የመርፌህ ሰዓት ደርሷል ተነስ ሂድ ነው እምልህ !

ዘርፉ

(ገባኝ እንደማለት ያህል -) እምም . . . . . .

ተኮላ

(ወደ ጠርሙሷ አልፎ ብድግ ያደርጋትና የፔኒሲሊን እንክብል እሚውጥበት ውሀ እንደሌለባት ሲያውቅ እዚያው

ጣል ያደርጋትና በደረቁ ይውጣል ። ወደ ዘርፉ መለስ ይልና -) አባነንከሁ ? (ዘግየት ብሎ -) ሳምንት ቅዳሜ ዐድዋ ነበርኩ ።

ዘርፉ

(አልገባውም -) የት ?

ተኩላ

ዐድዋ ! ሲኒማ አታውቅም ለካ ! . . . አየህ ፡ ጐበዙ እንዲህ እንዳንተ አድፍጦ ተኝቶ ነበር ። ኤልቪስ ነበረች ጐበዟ ! ሳምንት ዐድዋ ኪታራዋን አልያዘችም ። ግን ግራና ቀኝ ኮልቷን አጭቃለች ። ጠላ ቷ አላያትም ። (እያስታወሰና እያስመሰለ እንቅስቃሴ በተመላው ስሜት ያሳየዋል -) ሬካርዶ ሞንታልባን ነበር ጠላቷ ። ድሮም ገዴ አደለም ፡ ሳየው ያበሽቀኛል ። ገና በመስኮት ብቅ ሲል ቀፈፈኝ ! ድሮም «ቀፈፌሽን » ነው እሚያስይዘኝ ።

ዘሎ ሲገባ መብራቷን ጥፍት አረገችበትና ለጥ አለች ። ጠላቷ ደነገጠ ። አሠጋው ። ወኔ ከዳው ። ይርበተበት ጀመረ ። ሽጉጡን አቀባብሎ እንደያዘ ሲቁነጠነጥ ከወምበሩም ከጠረጴዛውም ይጋጭ ጀመር ። ኮሽ ባለ ቁጥሩ እየደነበረ ሲተኩስ ፡ ሲርበተበት ፡ ሲተኩስ ፡ ጥይቱን ጭርስ ። ጐበዟ ሆዬ ይኸኔ መብራቷን ተግ ! ምን ይዋጠው እንግዲህ ያ ብሽቅ አፉን ከፍቶ ሲቀር አይታ የግራ ጐን ሽጉጥዋን መዘዝ . . ርጋ ወረወረችለት ። አንሳ አለችው ! ሲፈራ ፡ ሲቸር ፡ ሲር



በተበት ፡ ሊያነሳ ጐንበስ አለ ። ሽንጧን በሁለት እጅዋ ይዛ በፎርም ጠበቀችው ። አንሳ አለችው ! ብድግ አርጐ ሊተኩስባት ሲያነጣጥር የቀኝ ጐንዋን ሽጉጥ እንደመብረቅ ላጥ አርጋ እጁን ነድፋ አስረገፈችው ! ደሙን እየዘራ ሲንቀጠቀጥ ሽጉጥዋን አሽከርክራ በግራ ጐንዋ ሻጥ አረገችና «ተናዘዝ» አለችው ። አናዝዛ ፡ አስለፍልፋ ፡ አስወትውታ ፡ ሲበቃት ፡ ንቃው ፡ ገላምጣው ፡ ትታው ፡ ዞር አለች ። ይኸኔ ዝቅ ብሎ የወደቀውን ሽጉጥ ብድግ ሲያረግ ጥላውን አይታ መለስ አለችና በግምባሩ ፡ በደረቱ ፡ ስትቆጥርበት ጊዜ ተንደርድሮ ባፍጢሙ ተዘረረ ። ሬሳውን ታዝባ ፡ የያዘችውንም የወደቀውንም ሽጉጥ ቀለብ አርጋ ፡ በጣቶችዋ ላይ እንደእንዝርት ካሽከረከረቻቸው ባኋላ ፣ በግራና በቀኝ ጐንዋ ቂቅ አረገቻቸው ። ሳቅ ብላ እያፏጨች ውልቅ አለች . . . . ከቆንጆዋ ጋር በዜንጥ ተሳስማ ፡ ፈረሷ ላይ ጉብ ብላ ሽመጠጠች ።

ዘርፉ

(አሁንም ምንም አልገባው) ምንድነች እሷ በል ?

ተኩላ

(በንዴት -) ኤልቪስ !. . . ሲኒማ አይገባህም እንዴ ! (ዘግየት ብሎ ፡ እንደማሾፍ) ከእንቅልፍ አባነንኩህ እንዴ ?

ዘርፉ

እ ?

ተኮላ

አባነንኩህ ወይ !

ዘርፉ

(ይቅርታ በመስጠት አንደበት -) አይ ግድ የለም ኧረ ።

ተኮላ

(ወዲያው የፌዝ ትዊስት እየጨፈረ -) ግድ የለም ግድ የለም ፡ ታራራራ — ግድ የለም ታራራራራ ! ሰው እንዳይሆን የለም ፤ አሃሃሃ ! ሰው እንዳይሆን የለም ፥ ቲሪሪሪም !

ዘርፉ

ወንድምህ የት ጠፍቶ ይሆን እያለ ሲሠጋ ነው ያደረው ።

ተኮላ

(በማሾፍ -) ነው ? . . . . ቲሪሪሪም ቲቲም ታራራራ !

ዘርፉ

አዎን ። (በትዕዝብት ያስተውለዋል -) ምንድ ነው እሱ ቅድም የዋጥከው በል ?



ተኮላ

የራስ በሽታ መድኀኒት ይሉታል ፤ ለጨጓራ ቁስል አይበጅም ። . . . . ፊትክን ታጠብክ ? . . . . . . ቲሪሪም ቲቲም ታራራ !

ዘርፉ

አዎን ፤ መቸም እንደነገሩ ።

ተኮላ

ቁርስ በላህ ? (ጭፈራውን አቋርጦ በዚያው ስልት እያፏጨ ዳቦዋን ብድግ አርጐ ይገምጣል ።)

ዘርፉ

ኧረ የለም ምንም አላሰኘኝ ። (ዘግየት ብሎ -) ወይ ደሞ በእንቁላል የተቦካ ይሆናል ። ምኑ ቅጡ !

ተኮላ

አዎን ፤ ምኑ ቅጡ ፡ ምኑ ቅጡ ፡ ምኑ ቅጡ ። (በማሾፍ ያነበንብ ይጀምራል -) የእንቁላሉ ፤ የዘይቱ ፤ የቅጊቱ ፤ የላቦቱ ፤ የጉድፉ ፡ ምኑ ቅጡ ፡ ምኑ ቅጡ ! ባለሞያ አላቦካው ! ባለሞያ አልጋገረው ! በዚህ ላይ ፤ ለፉርኖ ፤ ለብስኩት ፤ ለቂጣ ፤ ለማካሮኒ ፡ ለባስታሹታ ፡ ለሙቅ -ለአሹቅ ፡ ይሸጣል ይሸቀጣል ። ከምድር ወጥቶ እምድር እስኪገባ ድረስ ባለሞያ አይነካው ! ርዝራዡ ፡ ወፍ ዘራሹ ፡ ሲፈጭ ሲሰልቀው ፡

ሲያቦካ ሲያገነፋው ፡ ይውላል ! ኧረ ምኑ ቅጡ ! (ድምፁን አለዝቦ ድንገት ወደ ዘርፉ ዞር ይልና -) ፍራሼ ተስማማህ?

ዘርፉ

እ ?

ተኮላ

ፍራሼ ተስማማህ ወይ !

ዘርፉ

(በማሰላሰል -) እምም . . . ። አዎን ፤ አዎን ፤ ተመችቶኛ ፤ ድንቅ ነው ። . . . . . ታዲያ እኮ ወንድምህን - ይኸ ምንድ ነው እምትሉት - መከዳ ወምበሩ እንኳ ይበቃኛል ብየው ነበረ ።

ተኮላ

(የፌዝ ቃና በተመሳቀለበት አንደበት ይግደረደራል -) እ ማይሆነውን ! እንዴት ፤ ለምን ተብሎ ! የማይደረገውን ! እኮ ነጆህ እያሰህ ? የሰይጣን ጆሮ አይስማው ! ልጅህ እኮ ነኝ ! «የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ» ትሉ የለ ? አንተ ፍራሿ ላይ ፡ እኔ ወምበሯ ላይ ፡ ነው እንጂ ። አለበለ ዚያማ ነውር ነው ! እንዴት ተደርጎ ? የማይደረገውን ! . . የመኪናዎቹን ቅዝቃዜ ተላመድከው ?



ለዝቦ ድን

ግት ዞር ይልና . . . ነው የምትሄደው ?

ዘርፉ

እ ?

ተኮላ

ቅዠቱን ተላመድከው ወይ !

ዘርፉ

አይ ፡ ምንም አይል ። ደግ ነው ፤ ኧረ ምንም አይል ።

ተኮላ

አዎን ምንም አይል ፡ ይለመዳል ። የማይለመድ የለ ። (ከደረት ኪሱ የሲጋራ ብጣቂ አውጥቶ ፤ ክብሪት ጭሮ እያጨሰ -) ሲጋራ እንዳልጋብዝህ አልለመድክም ! ( አጭር ፀጥታ ። ይተያያሉ ። ዘርፉ ከመሩጠጥ አንገቱን ደፉ ያደርጋል ። ምነው እምትነግረኝ ነገር ነበረህ ? . . . . . እ ?

ዘርፉ

(በማቅማማት -) አይ የለም ኧረ ።

ተኮላ

ዚኝ ጎ . . . .
የመኪናዎች, . .

ዘርፉ



ተኮላ

አንተም ትረሳለህ ? ወንድሜ ብቻ መስሎኝ ነበር እሚረሳ ። የወንድሜ ችግሩ ነገር መርሳቱ ። ነርቭ እሚሉት በሽታ ሰምተህ ታውቃለህ ? የደም ሥሮች መታወክ ነው ይላሉ ። የደም ሥርህ ሲታወክ ፤ ጭንቅላትህ ይታወካል ፤ ጭንቅላትህ ሲታወክ ፤ አእምሮህ ይታወካል ፤ አእምሮህ ሲታወክ ፡ ወፈፍ - ወፈፍ ያረግሃል ፡ ወፈፍ - ወፈፍ ሲያረግህ . . . ደግ አይደለም ። ወንድሜ ወፈፌ ነበር ። ነበርም ፡ ነውም ። አልፉ አልፉም ትጥለዋለች ። አስተማሪ ሲደበድበኝ ለምን ተከላከልክ ይለኛል ? ከትምህርት ቤት ሲያስወጡኝ ለምን ወጣህ ይለኛል ? ሚስቱ ከነልጅዋ ጥላው ከሄደች ከሩቅ ተለውጧል ። በርራ ሄዳ የቤት አዳሪ ገረድ ሆነች ፡ እህታችን ናት አሉ ያስቀጠረቻት ። እህታችንማ ቤት አዳሪነቱን ጥርሷን ነቅላ አርጅታበታለች ። ታዲያን አላለፈላትም ። . . . . . . . . . - - -

በቀደም መታከሚ ልትበደር ሄደህ አብርራህ የለም ! የወንድሜም ሚስት ወደዚያው ግድም ናት ። እሷም ጋ ዘመድ ነኝ ብለህ ሄደህ አልነበር ? ዳሩ ምን ይሁን እሷም አበረረችህ ። አንተን የማያበርህ የለ ! . . . . .እንኳን አንተ እርስ አይደርስባትም ። እንዳይደርስባት በቁስ አስገዘተችው ፡ በሕግ አስፈረመችው ። እሱ ግን እያሾለቀ ልጁንም እሷንም ያያል ። ሆኖም ከሩቅ ተለውጧል ። (ድምፁን አስገቦ ዩን ግት ዞር ይልበትና) መቼ ነው የምትሄደው ?

ዘርፉ

የት ? . . . . ሐኪም ቤት ?

ተኮላ

(በሻከረ የንደት አንደበት -) ሐኪም ቤት እንጂ ሌላማ የት ትሄዳለህ ! (አጭር ፀጥታ ። ዘርፉ ቀና ብሎ ያየውና ዓይን ላይን ሲጋጠሙ አንገቱን ቀለስ ያደርጋል -) ምነው ፤ ልት ነግረኝ የፈለግኸው ነገር አለ ?

ዘርፉ

(በማቅማማት -) አይ የለም እረ . . . . .

ተኮላ

እረ ?

ዘርፉ

አስቤ ነበር ፤ እረሳሁት ።

ተኮላ

(ቀበል ብሎ እየተቁነጠነጠ ያነበንባል ። ) የወንድሜም ችግሩ ነገር መርሳት ነው ብዬሃለሁ ። ትዝታው ሁሉ አልፎ አልፎ ሰላቢ የሰለበው ይመስል እልም ጭልጥ ይላል ። (ዘርፉ ከኪሱ ቦርሳ ውስጥ የወደቀውን ፎቶግራፍ ያይና ሂዶ ። አየት ያረግና) አዎን ፡ ለምሳሌ ይኸን መከረኛ ፎ



ቶግራፍ ከቦርሳው ውስጥ ፡ ከብብቱ ውስጥ ፤ ለይቶት አያውቅም ። አሁን ግን ይኸው ጥሎት እረስቶት ሄደ.ል ። ተለይቶት አያውቅም ። የልጁ ፎቶግራፍ ነው ። ቢሮም ሆኖ ወጣ እያረገ ያስተውልና ነው ሌሎ መልሶ እሚከተው ። አንዳንዴማ ሌሊት አልጋው ላይ እየተገላበጠ ሕያው ፍጡር ይመስል ፎቶግራፉን ታቅፎ ሲያባብለው ያድራል ። ከበድን ወረቀት ጋር ሲያወጋ ከሰማኸው አልተለወጠም ብለህ ታምናለህ ? (ዘርፉ እጁን ዘርጋ ሲያደርግ ፎቶግራፉን አልጋው ላይ ይወረውርለትና እየተቁነጠነጠ ይቀጥላል ።) ይኸኔ ፎቶግራፍ ፍሬም ማምረያ ቤቱን መዞርዞሩ ያመሳቅላል ። እኔን ወንድሙን ማሳደግ ሳይችል ሌላ ተቀጥላ አብቅሎ ይዋልላል ። በዚህ ላይ ሽንቁር ጫማ ሰክተህ ተደናቀፍ ይለኛል ።

ዘርፉ

(የልጁን ፎቶግራፍ አስጠግቶ እያስተዋለ በአድናቆት -) እሰይ ! እሰይ ! እሰይ . . . (ተኮላ ምን አገኘ ብሎ ወደሱ መለስ ሲል -) እንዲህ ነው ልጅ ! እንዲህ ነው ልጅ ! (ፎቶግራፉ ላይ እትፍ እትፍ ይላል -) ያሳድግህ ! ልክ አባታችሁን ቁጭ እኮ ነው ! የሞገስን አባት በውን ተመስሎ እደል እንዴ የወጣው ?

ተኮላ

(ዘማየት ብሎ በማሾፍ አንደበት -) እረ ?

Scanned by CamScanner

ዘርፉ

የሽፋሉን አወራረድ አየህልኝ ? የገጼሳ ፈካ ማለት ? አባታችሁ ዳግመኛ ተመልሶ መጣ ማለት እኮ ነው ።

ተኮላ

(በማሾፍ እንደበት -) ነው ?

ዘርፉ

እንዴታ ! (እንደገና ፎቶግራፉን መልከት ብሎ -) እንዴታ ! (ወዲያው በትዝታ ገጽ ተከዞ ብሎ -) አባታችሁ ጀግና ነበረ ። አገር የቀናበት ብርቱ ገበሬም ነበረ ። አባታችሁ ያፈርን ጣዕምና ጥቅም ቀምሶ የሚለይ ብርቱ የእርሻና የመከር ሰው ነበረ ። በዚህ ላይ ከጀግኖች ጀግና ፥ ከወንዶች ወንድ ነበረ ። «እንዴት አንተ እኔ የዳኘው ባርያ» ብሎ ግምባሩ ኮስተር ካለ ፥ ብርክ አስይዞ ምድር ተቀዳ በዋጠቺኝ ነው እሚያሰኝ ። ቁመናው እንኳን አሁን እንዲህ ኮስምኜ ያኔም ከኔ ዘለግ ፥ ደንደን ብሎ ፥ ትከሻው ደሞ እንዲሁ እንዳንተው ቢሆንም ፥ የሱ ግርማ ሞገስ ነበረው ። ዐድዋ ሊዘምት ዳኘው ምኒልክ «ምታ ነጋሪት ! ክተት ሠራዊት ! ሏንቅህን ባህያህ ! ዐመልክን በጉያህ !» እያሰኙ አዋጅ ሲያስነግር -እኔ ያኔ ገና ጡት መጣሌ ነበር ፥ እሱም ገና ለሴት ያልደረሰ ጋሜ ነበር - ከአባታችን ጋር ካልዘመትኩ ብሎ ሲያቅማማ እንደ ሕልም ትዝ ይለኛል ። ለማይጨው ጊዜ ግን ፥ እኔ ያባባን ወጨፎ አንግቼ ፥ እሱ ከሽፍታ የማረካትን



ጐራዴ ይዞ ከበቅሎዋ እኩል እየሰገርን ካባታችን ግራና ቀኝ ሆነን ነው የተሰለፍነው ። ጦር ሜዳም ላይ ቢሆን ፥ እኔን እንኳ የፍርሃት ሲቃ ይዞ ሲንረኝ ፥ እሱ «አይዞህ የናቴ ልጅ !» እያለ ነው እንደግሥላ እየተወረወረ ሲናደፍ አባታችን ፊት የወደቀው ።

ተኮላ

(ጭራውን አንስቶ አልጋው ላይ ተወርውሮ ይወጣና እግሬው ደምብ ላድ ቁጢጥ ብሎ ጭራውን በፌዝ እየወዘወዘና ዘርፉን ቁልቁል እያስተዋለ እንደዋዛ -) . . . . . . .
ለምን ነበር የመጣኸው ? . . . ተወዉ ዳሩ እኔም እንዳንተው ዘንግቼው ነው ። መርዶ ልታረዳን ነበር የመጣኸው ።

ዘርፉ

(እንዳልሰማ ይቀጥላል -) አባታችሁ ወንድ ነበረ ። ከዚያም ፊት ፥ በሰላሙም ጊዜ ፥ ጨዋ ፥ ጸሎተኛ ፥ ብርቱ ገበሬ ነበረ ። ዶሮ ከቆጡ ሳይወርድ ከመኝታው ተነስቶ ፥ ወፍ ሳትንጫጫ አስቀድሞ እያፏጨ ፥ ፀሐይ ሳትፈነጠቅ ሞፈር ቀምበሩን ተሸክሞ በሬዎቹን እየነዳ ፥ ያን ጥቁር መስኖ ተልም ሲያስመስለው ይውላል ። የገበሬዎች ሁሉ ከእንቅልፍ መቀስቀሻ ያባታችሁ ጅራፍ ጩኸት ነበረ ። እህል በጐተራው ፥ አዝመራ በማሳው ፥ ከብትና ፈረስ በጋጣው ፥ እንጀራ በመሶቡ ፥ በግና ፍየል በጉረኖ ፥ እንደተጣበበ ነበረ ። አባታችሁ . . . . . . . . .

ተኮላ

(ያቋርጠውና በመሠሪ ከናፍሩን የጐን ገልፈጥ አርጐ በዋዛ አንደበት -) እሱን ተወውና መቼ ነው እምትሄደው ?

ዘርፉ

(ደንገጥ ብሎ -) እ ? (ቀና እላለሁ ሲል በስቃይ ሆዱን በሁለት እጆቹ ደግፎ ያምጣል ።)

ተኮላ

(በንዴት ብድግ ይልና ቁልቁል እያስተዋለው ጮክ ብሎ-) መቼ ነው የምትሄደው !

(የመድረክ መብራት በፍጥነት ይጨልማል ።)



ለ

ከሁለት ደቂቃ በኋላ ። መብራት በዝግታ ሲበራ የተሊላ ሳል ይሰማል ። ተኮላም ዘርፉም ከነበሩበት አልተንቀሳቀሱም ። ሞገስ ይገባል ።

ሞገስ

(ተኮላ መኖሩን ሳያይ -) አንድ ዕቃ ጠፍቶብኝ ነው የተመለስኩት አብዬ ፤ እዚህ ጥየው ይሆን ? (አቋቋማቸውን ሲያይ ዞር ብሎ ወደነሱ መለስ ይላል -) ምን ሆናችኋል ? (ተኮላ ካልጋው ላይ ጡብ ብሎ ይወርድና መለስ ሳይል ውልቅ ብሎ ይወጣል ።)

ዘርፉ

(ፎቶግራፉን ከሆዱ ጋር ደግፎ ይዞት ነበርና እጁን ዘርጋ አርጐ -) ይኽ ይሆን የጠፋብህ ዕቃ ?

ሞገስ

(በችኮላ ቀበል ብሎ መልከት ያረገውና -) ነው ። (ዘግየት ብሎ በፍስሐ አንደበት -) ምን ሳረግ ጣልኩት ይባላል ? (ቦርሳው ውስጥ በጥንቃቄ እያስቀመጠ -) አሁን እኮ ቀልብ እያሳጣ ቢያስቸግረኝ ፍቃድ ተቀብዬ መምጣቴ ነው ።

ዘርፉ

(ሲፈራ ሲቸር -) አንድ - ሦስት ብር ያህል ይዘሃል ሞገሴ ?

ሞገስ

እረ አላያዝኩም ። ያለቺኝን ቅድም ለተኮላ ሰጠሁት ። ፎቶግራፉም ያኔ ነው መሰለኝ የወደቀብኝ ። ምነው ደህና?

ዘርፉ

አይ ፡ ያው ሐኪሙ ነዋ ። የሚዋጥ መድኃኒት ግዛ ብሎ ደሞ ወረቀት ቆረጠልኝ ። . . . . የካሁን ቀደሙንም አልከፈልኩህ ።

ሞገስ

ግድ የለም እረ ቀስ ብሎ ይከፈላል ። (አጭር ፀጥታ ። የተሊላ ሳል ይሰማል ። ሞገስ ዘግየት ብሎ በማቅማማት -) አንድ ጉዳይ ላማክርህ ብዬ ነበር አብዬ . . . . . . (አጭር ፀጥታ ።)

ዘርፉ

(ደስ የሚያሰኝ ነገር ድንገት ትዝ ብሎት በፍስሐ አንደበት -) እኔም አውቄዋለሁ ሞገስዬ ! የምትነግረኝን ምሥራች አስቀድሜ አውቄዋለሁ ። እኔ ያሰብኩትንማ ከሆነ የምትነግረኝ ምሥራች እውነትም የማርያም ልጅ ባርኮሃላ ! እውነትም ወልደ አብ ባርኮሃላ ! (ወደ ሞገስ ቀረብ ለማለት ሲቃጣ ሞገስ በዝግታ ጀርባውን ያዞርበታል ። እሱም ቆም ይላል ።)



ሞገስ

(ዘግየት ብሎ በቦዘነ አንደበት -) ምሥራች አይደለም ። የከተማን ኑሮ ትቼ አባታችን ርስት ላይ ተመልሼ ገበሬ እሆናለሁ እምልህ መስሎህ እንደሁ ፡ ተሳስተሃል ። . . . . ገጠር ገብቼ ገበሬ እሆናለሁ ብልህማ እምፈልገውን አወቅሁት ማለት ነበር ።

(ዘርፉ ቅር ብሎት ወደ አልጋው ተመልሶ ቁጭ ይላል ። ሞገስ ከአጭር ፀጥታ በኋላ ይቀጥላል ።) አብዬ ፡ እኔና ብጤዎቼ የምንፈልገውን አናውቀውም ። እኛ የዛሬዎቹ ፡ መሠረት ሳንይዝና ሥር ሳንሰድ እንደሙጃ አረም ከየጥሻው ላይ የምንመዘዝ የጉድ አዋጅ ተክሎች ነን ። አንተ የምትፈልገውን ታውቀዋለህ ፤ ይኸን ማወቅ መታደል ነው። እኔ ከየት እንደመጣሁ ረስቼዋለሁ ፡ የት እንዳለሁ አይታየኝም ፤ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም ። ይህ መረገም ነው።. . አብዬ ፤ አለቃዬ ፡ ጨዋ ፡ ሽማግሌ ሰው ነው ። አንዳንዴ ችግሩን እንደጓደኛው እያጫወተኝ ፡ «ይኸውልህ ሞገሴ የኑሮዬ እንቆቅልሽ ፡ መፍትሔውን ታገኝልኝ እንደሁ ብዬ ነው እማዋይህ» ይለኛል ። በቀደም ማታ «ገረዴን ላገባ ነው ሞገስ ፤ ምን ይመስልሃል ?» አለኝ ። «እየተልከሰከ ስኩ ትራፌ መቃረሙ ሰለቸኝ» አለኝ ። «ዘመድ ተጠያይቆ ያመጣልኝ ባለሞያ ናት» አለኝ ። ትላንት ለምሳ ቤቱ ይዞኝ ሄዶ ባለሞያነቷን ለማስመስከር ፤ የሠራችውን የዶሮ ወጥና ምንቸት አብሽ ጋበዘኝ ። የጠመቀችውን የገብስ ጠላ ቀመስ እንዳደረኩት ጀርባዬን ላብ አሰጠመኝ ። ገበታውን

አቅርባልን ፤ ስሜቷን ፀጥ አርጋ ፡ ሽሽጋ ፡ ወደ ጓዳዋ ተመለሰች ። . . . . ገረዱ የኔ ትሁኔ መሆኗን አላወቀም ። ሚስቴ እንደነበረች አላውቀም ። ከምሳ በኋላ ወደ ቢሮ ስንሄድ ፡ እግረ መንገዳችንን ፡ «ታድያን ምን ይመስልሃል ሞገሴ» አለኝ ። (ዘግየት ብሎ -) ምን ልበለው አብዬ ?

ዘርፉ

(ቱግ ብሎ ይነሳና በምሬት -) በጥይት በለው ! . . . እንዴት አንተ ! በቤታችንም የለ ። «ባባት እርስትና በሚስት የለም ዋዛ !» ነው እኮ ከነተረቱ ። በጥይት በለው ! !

ሞገስ

(ሰምቶ እንዳልሰማ ተነስቶ ከመድረኩ በስተግራ ወረድ ብሎ በለዘበ እና በትካዜ አንደበት ይቀጥላል -) አለቃዬ ፤ አንድ የቄስ መምህር ቀጥሮ ፤ ከቤቱ ጀርባ ከፊፍ ሥር የመንደሩ ሕፃናት ተሰብስበው ይማራሉ ። ልጄንም ሕፃናቱ መሀከል አየሁት ። ሠሌዳውን ፊት ለፊት ዘርግቶ የፊደሉን ዘር በሳር እየጠነቆለ «አ - ቡ - ጊ - ዳ - » ሲል አየሁት። (ዘግየት ብሎ -) እሱ ግን አላየኝም ። ቢያየኝም አያስታውሰኝ ። ሕፃን ሰላ ነው ትሁኔ ይዛው ወጥታ የቀረችው ። አለቃዬ ፤ «የልጅዋ ስም ድጋፌ ነው ፤ አልፋ አልፋ ይጥና ትለዋለች» አለኝ ። «ያባቱን ስም እንዳልጠራ ምያለሁ ብትለኝም እሷም የምታውቀው አይመስልም» አለኝ ። «እኒህ ሴት አዳሪዎች የስንቱን አባት ስም ያስታውሱታል ብለህ



ነው ሞገሴ !» ብሎ ሳቀ ። ልጁ ግን ያሳሳኛል ይላል ። አባዬ ብሎ በሮ ሲጠመጠምብኝ ልቤን ይከፍለዋል አለ ። (ዘግየት ብሎ -) . . . . ምን ይሻላል አብዬ ?

ዘርፉ

(በታላቅ ምሬት -) ሞት ! ሞት ይሻላል ! !

ሞገስ

(ካጭር ፀጥታ በኋላ አሁንም ሰምቶ እንዳልሰማ በትካዜ ይቀጥላል -) አብዬ ፤ ትሁኔ ፡ ዛሬ ጠዋት ቢሮ ድረስ የነፍስ አባታችንን ላከችብኝ ። «ልጁም እንዳይማርና እንዳንተው ባክኖ እንዲቀር ካላሰኘህ በስተቀር ፤ እኔም ከምቹ ትዳሬ ተፈናቅዬ ዳግመኛ ወደ ሴት አዳሪነቴ እንድመለስ ካላሰኘህ በስተቀር ፤ ሁለተኛ እንኳን ቤቴ በበሬ ዝር እንዳትል ብላሃለች» አሉኝ ። እኔም ዳግመኛ ላልደርስባት ፡ መስቀላቸውን ጨብጨ የመሀላ ቃሌን ሰጠኋቸውና ሄዱ ። (ዘግየት ብሎ -) አብዬ ፤ ልጄ ፡ እኔ ከቶውኑ ላለብሰው የማልችለውን ልብስና ጫማ ለምዶአል ። ከቶውኑ ልገዛለት የማልችለውን አሻንጉሊትና መጫወቻ ቢስኪሌት ለምዶአል። ከቶውን ላበላው የማልችለውን የምግብ ዓይነት ለምዶአል ! አብዬ ፤ . . . . . .

ዘርፉ

እረ በጉበዝ አምላክ አብዬ አትበለኝ ጃል ! (በመገረም አን

Scanned by CamScanner

ደበት -) እሳት ዐመድ ወለደ ! እሳት ዐመድ ወለደ ! እንዲህ የቁም ተዝካርህን ከምትበላ ሚስትህን ከነልጅህ አሥረህ ወስደህ ያባትህን ርስት አትበላም ! የጀግና ልጅ እኮ ነህ ! ወንድ አደለህም እንዴ ! . . . እንዴት አንተ ! ያባትህ አጥንት ሾህ ሆኖ እንዳይወጋህ ! ወንድ አደለህም እንዴ ?

ሞገስ

(ዘግየት ብሎ በመድረኩ መሀል ፊትለፊት ይዘልቅና -) ወንድ ማለት ምን ማለት ነው አብዬ ? የወንድ ትርጉሙ ከቶውኑ ሳይገባኝ አለ ። እንደእሳት እራት ነበልባል ውስጥ መክሰት ነው ? እኛ የዛሬዎቹ አብዬ ፣ ወኔአችንን እንደኤሊ እንደ ቀንድ አውጣ ፣ ቅስማችን ውስጥ ቀብረን ነው ከዕለት ወደ ዕለት የምንጐተተው ። አባቶቻችን ስትተርቱ «ማን ነበረ ቢሉ የተሰበረ ፣ ማን በላ ቢሉ የቀበረ» ትላላችሁ ። አዎን አብዬ ፣ ውሀ ቀጠነ ብሎ ሲቃ ቢያንቀውንፋስ አፍኖ ገደለው ፣ ነው ወጋችን ።

ቀድም እንዳልኩህ እኔና ብጤዎቼ ሥር ነክሰን የጠጠርንጽኑዎች ፣ መከራ ቀልቶ ያደነደነን ብርቱዎች ሳንሆን ፣ መሠረት ለቅቀን የምንፈረጥጥ የሆያ ሆዬ ጉብሎች ነን ። እንደ ጌጥ ዕቃ ተሽልመን በየአደባባዩ ለላንቲካ መታየታችንን እንኳ ለተፈጥሮ ውለታ እንደዋልንለት ያህል ቆጥረን ፣ ይኸን ሠራሁ ማለት ካፋችን ሳይወጣ ፣ ይኸን ሠሩ በማለት ብቻ ምላሳችን የሚቀጥነው እንበዛለን ። ዛሬ ፣



ሰማየ ሰማያት በደመና ነጐድጓድ ሳይሆን በሰው ሠራሽ ሞገደ ፍላፃ ጥቀርሻ ለብሶ ሲያከናንበን እያየን ፣ እጃችን በሥራ ከሚፈጥን ይልቅ በጭብጨባና ባስረሽ ምቺው ተወራጭቶ እንዲዝል ሾተላይ ተጥሎብናል ልበል ! (ዘግየት ብሎ -) ያባባ አጥንት እሾህ ሆኖ የሚወጋኝ ፣ እሱ ለኔ ሊያደርግልኝ ይመኝ የነበረውን በጎ እኔ ለልጄ ያልተመኘሁለት እንደሆነ ነው ። ልጄ ፣ ይጥናዬ ፣ ሲለየኝ ፣ የኔን ያባቱን ያህል የማንም አንጀት አይቆስል ፣ ነገር ግን አንጀቴ እንድያውን የሚበጠሰው ፣ ዛሬ ዕጣ ክፍሉን ያስገኘለትን የምቹ አስተዳደግና የትምህርት ዕድሉን ያደናቀፍኩበት እንደሆነ ነው ። (አጭር ፀጥታ ። ወደ ሶፋው ተመልሶ ጫፉ ላይ ይቀመጥና ፣ መሀረቡን አውጥቶ ግምባሩን ከጠረገ በኋላ ፣ ፎቶግራፉን ከቦርሳው አውጥቶ እያስተዋለ -) ምን ይመስልሃል አብዬ ? . . . . .

ዘርፉ

(ዘግየት ብሎ ከተቀመጠበት ይነሳና ሞገስን በንቀት እያስተዋለ -) መረገም ! መረገም ይመስለኛል ። አንተም ብለኸዋል ፣ መረገም ነው ፣ በቃ ። (ግራ ገብቶት ዘግየት እንዳለ ወደ ሞገስ ጠጋ ብሎ ጐኑ ይቀመጥና በምክር አንደበት -) ልጄ ፣ የሚነግሩህን ስማ ። ልጅህንና ሚስትህን ከምትሸጣቸው ወደ አባትህ ርስት ይዘሃቸው ሂድና በግምባራቸው ወዝ ይደሩ ። ቃለ እግዚአብሔርም የሚያዘው ይኸንኑ ነው ሞገሴ . . . (ሞገስ በብስጭት ካጠገቡ ፈንገጥ ብሎ

ራቅ ብሎ ጀርባውን አዞሮበት ይቆማል ። ዘርፉ ቆጣ ብሎ
ይቆጥላል -) የልክፍታ ነው የበሽታ ! ጤና የለህም ልበል !
ጤና ነስቶሃል ልበል !

ሞገስ

(በንዴት ዞር ይልበትና እንዳይጮህ ጥርሱን ነክሶ -) አብዬ
ተው ጤና የለህም አትበለኝ ! የሰማ ኸውም ቢልት እንዳለ
እርሳው ። (በመጠኑ ለዘብ ብሎ -) ደሞ ባታማክረኝም
ተወው ! ጤና የለህም አትበለኝ ! ! (እንደገና ጀርባውን
አዞሮበት ይቆማል ። ረዥም ፀጥታ ።)

ዘርፉ

(አንገቱን ቀልሶ በጸጸት አንደበት -) እኔስ እሺ ምንም አል
ልህ ። . . . . አንተም አማክረኝ አትበለኝ ። በቃ ። (አጭር
ፀጥታ ። ዘርፉ በብስጭት እተቀመጠበት ሆኖ ይቁነጠነ
ጣል ። ከወለሉ ላይ የሣር ጉድፍ ያነሳና በፊት ጥርሶቹ ላይና
መሃል ይዞ ይሰነጥራታል ። ከሁለት ገምሶ እያንዳንዷን በየ
ተራ እትፍ ይላታል ። ይቁነጠነጣል ። ወዲያው ፡ በመገረም
አንደበት -) ሆሆይ ! (ዘግየት ይልና -) ሆሆይ ! (ዘግየት
ብሎ -) የጤናማ ካልሆነ የስካር ነው ። የልቦና መሳከር
ነው ። የወኔ ፡ የልቦና ፡ መሳከር ነው !



ሞገስ

(ጀርባውን እንዳዞረበት ነው ። ንዴቱ በርዶም ስላልበረደ
አልፎ አልፎ እፍን እያረገው -) እሱንማ ምነው ነግሬህ ። የ
ተሳከረችዪቱ ሥልጡን ዓልም ዘንካታዎች ነን ብዬህ ። እን
ደሐረግ ሬሣ ባጉል ልማድ ላይ የምንጠላጠል የጉድ አዋጅ
ነን ብዬህ ። ምነው ፡ ሥር ሳንሰድ ከየፍጉ ላይ ተመዘን ባን
ገት በላይ መመጻደቅ ብቻ ሰማይ ለመቆቀስ የምንቧጥጥ
የአረም ርዝራዦች ነን ብዬህ ። (ጥቂት ዘግየት ብሎ ፎቶግ
ራፉን ፊት ለፊት ይዞ በናፍቆት እያስተዋለ ሲቃ ይተናነቀ
ዋል ። ወዲያው ወደ ዘርፉ ድንገት ዞር ብሎ ከውስጡ የሚገ
ነፍለውን ሰቀቀን አፍኖ ለመያዝ እያማጣ -) የልጄንም ዕድ
ል እንደኔው ስንኩል እንዳላረጋት ብዬ ነው አብዬ ! ይጥና
ዬም እንደኔው ተቅበዝብዞ የጊዜ አጣቢ ሆኖ እንዳይቀር
ብዬ እኮ ነው አብዬ ! ልጄ እኮ ነው አብዬ ! ምን ይበጀኝ
ነው እምትል ! ? . . . . .

ዘርፉ

(ሞገስ እጆቹን ዘርግቶ ሊማለደው ለመቅረብ ይቃጣል ።
ዘርፉ እንዳይጠጋው በሩቁ በእጁ ይከለክለዋል ። . . . .
(በምሬት -) እኔ አላውቅም ! ! እኑ አላውቅም ! !
(ሞገስ ሽምቅቅ ብሎ መለስ ይላል ። ከአጭር ፀጥታ በኋላ
ገስ እንደተሸማቀቀ ሄዶ አንገቱን ደፍቶ አልጋው ላይ
ፍ ይላል ። ዘርፉ በትካዜ ተውጦ ብቻውን እንደሚናገር
ው በልዝብታ ያነበንባል ።) እኔ አላውቅም ሞገሴ ።

(ትንሽ ዘግየት ይልና -)
እኔ የማውቀው ያባቴን ነው ፡ ማልዶ ለመከር መነሳት
ሞፈር ቀንበር ይዞ መዝራት ፤ ጥቁር አፈር ገፍቶ መብላት።
ከእናቴ ማኅፀን ወጥቼ ፡ እሪ ብዬ ያረፍኩባትን
ተንከባልዬ አድጌ ፡ ባራት እጂ የቆምኩባትን
ጥቁር አፈርን ነው እማውቅ ፡ ጭሪ ምሼ እምበላትን ።
አባቴ እጂን ይዞኝ ስድህ ፡ እንኮኮ አዝሎ ሲያሯሩጠኝ
ጫጩቷን «እሽ» በል ሲያሰኘኝ ፤ ጥጃን «እምቧ» በል ሲያ
ሰኘኝ
አውድማው መሃል አንጋሎ ፡ ጨረሯን ከሩቅ ሲያሳየኝ
እዚያች ርስት ላይ ቆሞ ነው ፡ ሞፈር መያዝ ያስተማረኝ ።
አያቶችህ የሞቱባት ፡ አፅማቸው አፈር የሆነባት
አባትህ የተዋጋላት ፡ እናትህ ያረፈችባት
ያቺን አፈር ቸል አትበላ ፡ መጠሪያህ ወይ መረሻህ ናት ። . .
ጎህ ቀዶ ዳገት ሲወጋ ፡ ሠረቀ ብርሃኑን ሲሰጥም
ክረምት በበጋ ሲዋጥ ፡ ደመናው በጨረር ሲቀልም
የቅድም አያትህ ፈገግታ ፡ የቅድም አያትህ በጎ ሕልም
ጉልበቱ ላቡና ወዙ ፤ ያባቶችህ ደምና ቅስም . . .
ዶፍ ወርዶ ሲንፏፏ ጐርፉ ፡ በአውሎ ነፋስ ዛፍ ሲዛባ
የቅድም አያቶችህ ደስታ ፡ የቅድም አያቶችህ እምባ . . .
ከዚያች ከጥቁር አፈር ጋር ፡ ተቀምሞ ተመሳቅሎ
በትእዝብት ይጠብቅሃል ፤ ተው ልጄ እንዳትሸሸኝ ብሎ ።
ናፍቆቷ ከቶ አይለይህ ፡ ትዝታዋ ባይንህ ይጉላ
ከቤታችን ግርጌ ያለችው ፤ ኩሬ በጐርፍ ስትሞላ



Scanned by CamScanner

እየተንጠላጠላችሁ ፤ ታረግፏት የነበር ሾላ . . . . . . . .
መከር ገባ መከር ወጣ ፡ መሮጡ ደጋና ቆላ . . .
በናፍቆት እንጂ በንፍገት ፤ አትዩአት አለኝ አባባ ፤
ያቺን የወተት ጫጪዬን ፡ ያዘሉብኝን አንቀልባ
ስስቅና ሳለቅስባት ፡ ያሳደገችኝን አምባ
ከማኅፀን ዓለም ወጥቼ ፡ አፈር ዓለም እስክገባ
አትርሳት አለኝ አባባ ፡ አትራቃት አለኝ አባባ ፤ . . .
ጥቁር አፈር ወዙ ሲቀልጥ ፤ አረም ከላዩ ላይ ሲላጥ
በፀሐይ በታች ደመና ፡ ተጠልሎ በክንፉ ሲዋጥ
ባሻገር ኮረብታውና ፡ ሸለቆው ተውጦ በዱር
ምድሯ ጥቁር ፤ ሰማይ ጥቁር ፡ ባሕር ጥቁር ፤ ሕዝቧ ጥቁር .
ለምለም ሸማዋ ሲያላብስ ፡ ማሕፀኗ ሲሳይ ሲተፋ
ፍሬዋ ሕይወት ሲመግብ ፤ ጡትዋ አለኝታን ሲያፋፋ
ተንከባልሎ ላደገባት ፡ በገበናዋ ፈንድቆ
የሠረቀ ብርሃን ጮራ ፡ ሲያለብሳት ከሩቅ ፈንጥቆ
የተስፋ ፍሬ ሲፈራ ፤ ከማኅፀኗ ተፈልቅቆ
ያበቀለህ ወዛም አፈር ፡ ደጉ መጥጦት ሲገረጣ
«እጁ አፈር አይነካው ትውልድ» ፤ ሆኗል እያልክ የናንተ
ዕጣ
ያባቶችህ ዐፅምና ወዝ ፡ እንዴት ከጭብጥህ ይውጣ ! . . . . .
እኔ የማውቀው ያባቴን ነው ፡ ማልዶ ለመከር መነሳት
ሞፈር ቀንበር ይዞ መዝራት ፤ ጥቁር አፈር ገፍቶ መብላት።
(ረዥም ፀጥታ ። ዘርፉ ተመቻችቶ ይቀመጥና ይቀጥላል -)
እኔ የናንተን አላውቅም ፤ ጤ . . . ጤ . . . .ጤና ማጣት



ነው እሚመስለኝ ! . . . . . .

ሞገስ

(በታላቅ ንዴት ከተቀመጠበት ብድግ ይልና -)
እንጣላለን አብዬ ! ጤና ማጣት ነው አትበለኝ !

ዘርፉ

(እሱም ቱግ ብሎ -)
የጤና ማጣት ካልሆነ ፡ ታዲያን . . . . . . . . . .
(ብድግ እላለሁ ሲል ሆዱን በስቃይ በሁለት እጆቹ ደግፎ እንደታጠፈ ይቀራል ። ሞገስ ደንግጦ ቶሎ ቀረብ ብሎ ይደግፈዋል ። ዘርፉ በስቃይ ያምጣል ።

ሞገስ

(ደግፎ ሶፋው ላይ በጥንቃቄ እያስቀመጠው ድንጋጤ ባርበ ተበተው እንደበት -) አመመህ እንዴ አብዬ ! ጠናብህ እ ንዴ ? ቆይ አይዞህ ያንን ሁለት ብር ተበድሬም ቢሆን ላገኝ ልህ እሞክራለሁ ። (በጥንቃቄ ሶፋው ራስጌ ላይ እያስደገ ፈው -)
ቀስ . . ቀስ . . .
(የመድረክ መብራት በዝግታ ይጨልማል ።)

Scanned by CamScanner





## ሐ

ከሁለት ደቂቃ በኋላ መብራት በዝግታ ሲበራ ሞገስ የለም ። ዘርፉ ብቻውን ቅድም እንደነበረ እጅና እግሩን ዝርር አርጎ ሶፋው ላይ እንደተዝለፈለፈ ነው ።

ዘርፉ

(እንደተቀመጠ በቀኝ እጁ ተንጠራርቶ ሶፋው ራስጌ የተሰ ቀለችውን ክራር ያወርድና እንደበገና በመዲና ስልት እየ መታ ያንጐራጉራል -)

አፈር ብመስል እንኳን እንኳን . . . . . .
ሚቹ አለኝ ጓዴ ሚቹ አለኝ
ሚቹ አለኝ ጓዴ ሚቹ አለኝ
አፈር መስዬ ቢያየኝ ፡
አፈር ብመስል እንኳን እንኳን ።
አፈር ብመስል ምን ከፋኝ
ፈጥራ መግባ ብትበላኝ ?
ካፈር ተሰራሁ ካፈር በላሁ
የኋላ ኋላም ካፈር ገባሁ
አፈር መምሰሌን መቼ ጠላሁ ?
አፈር ብመስል እንኳን እንኳን ።
ሚቹ አለኝ ጓዴ ሚቹ አለኝ
አፈር መስዬ ቢያየኝ ፤ . . . . . . .

(ተኮላ በሩን ብርግድ አርጎ ጥልቅ ሲል ዘርፉ ክራሩን ስፍ ራው ይመልሳል ። ተኮላ ገብቶ ግትር ይልና ትንሽ ይቆያል። ዘርፉ አልጋ ላይ ይገነደሳል ። መጥፎ ሽታ የሸተተው ይመ

ስል ካንገቱ ቀና ብሎ ብርድ ልብሱ ላይ ያነፈንፋል ። ተመልሶ ይዘረረርበታል ። በሁለት እጆቹ ጭንቅላቱን ይደግፍና ጣራ ጣራውን ያስተውላል ። ይቁነጠነጣል ። ዘርፉ ከተቀመጠበት ይነሳና በአቶ ተሊላና በዚህኛው ቤት መጋጠሚያ መሀል ባለው በበስተጀርባው ግድግዳ ላይ የተወተፈውን የጨርቅ ውታፍ ሲነቅለው ከተሊላ ቤት ውስጥ ጢሱ ወደዚህኛው ቤት ውስጥ ይፈሳል ።

ዘርፉ ውታፉን ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠ -) ጕሽ እንዲህ ይሻላል እንጂ ። ቤቱ እንኳን ትንሽ ጢስ ጢስ ይሸተት እንጂ ። መቸም በውስጡ አልተጢሰበት ። (የተሊላ ሳል ይሰማል ። ተኮላ ከተጋደመበት ብድግ ብሎ ውታፉን ከጠረጴዛው ላይ ያነሳና ቀዳዳውን ይወትፈዋል ። ተመልሶ ይጋደማል ።)

ምነው ወተፍከው ተኮላ ? ቤቱ ጢስ ጢስ ይሸተት ብዬ እኮ ነው ። መቸም ቡና እንኳ አይቆላበት ። (የተሊላ ሳል ይሰማል ። ውታፉን ነቅሎ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጠዋል ።)

ተኮላ

(ሲንደረደር መጥቶ ይወትፈዋል -) ከዚያ ቤት የሚጢሰው ፡ ሳል ፡ ነቀርሳ ፡ ኢንፍሎኤንዛ ፡ ትኋት ፡ ብቻ ነው ! (ከአጭር ፀጥታ በኋላ ዘርፉ ውታፉን ነቅሎ ወደጠረጴዛው ሲንጠራራ ተኮላ ቀበል ብሎ ይወትፈዋል ። በዚሁ ዓይነት ሁለቴ ከተደጋገመ በኋላ በሦስተኛው ላይ ዘርፉ ውታፉን ጠረጴዛ ላይ



ለማስቀመጥ በመቃጣት ፈንታ ተኮላ እጅ ያስቀምጠዋል ። ተኮላ ውታፉን ብጭቅ አርጎ ወደ መሬት ይወረውረውና ተመልሶ ሄዶ ይጋደማል ። ዘርፉ ውታፉን ይጠጋግንና ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጠዋል ። የተሊላ ሳል ይሰማል ።

ተኮላ እንደተጋደመ አንገቱን ቀና አርጎ በትችት አንደበት -) ክራር መከርከር ታውቃለህና ! ክራር መከርክን አላወቅሁም ። እሱንማ ካወቅህ ትልቅ እንጀራ አለህ ፡ የወንድሜ ሚስት እተቀጠረችበት ትቀጠራለህ ። የሴት አዳሪ ገበያ አማጭ ትሆናለህ ። የመከርከር ተሰጥዎ እንዳለህ ብታውቅ በቀደም ዘመድ ነኝ ብለህ ስትሄድ ባላበረረችህ ። ድፍን ቂጭራ እፁብ ድንቅ ነው እሚልህ ። እሷም እንኳን ልታበርህ ታስተናግድህ ነበር ። እኔንማ አትወደኝም ። በሩቁ ፖሊስ ትጠራብኛለች ። ኡ ! ኡ ! የመጠጥ ጠርሙስ ይሰብርብኛል ትላለች ። ወፈፈ ማረጓ ነው ? ሲያልፍም አይነካኝ ። (ዘግየት ብሎ -) ወንድሜ የሚስቱን ታሪክ አዋየህ ? (ዘርፉ ዘግየት ብሎ በግምባሩ ብቻ አዎን ይለዋል ። ተኮላ ከመኝታው ብድግ ብሎ ጠረጴዛው ላይ የቀረችውን ደረቅ ዳቦ ይከክና ወዲያው መለስ ብሎ -) ታሪከኛ ናት ! ከሴት አዳሪ ግርድና ወንደ - ላጤ ግርድና ገብታ ... ወንድሜ አለቃ ነው ። እንዲህ አይምሰልህ ፡ ወዳጆች ናቸው ። በአአህታችን ናት አሉ ያስቀጠረቻት ። እሷም አትወደኝ ። በአባባ አጥንት አትድረስብኝ ነው እምትል ። የተቸረቸፈች ዕሩር ትመስይኛለሽ ስለምላት ነው ። ጥርሷን የነቀለችው በሴት አዳሪነት ነው ብዬሃለሁ ። አሁን አርጅታበታለች ።

ወንድሜ ስሚን እንዳያነሳ ምሏል ። እኔ ግን ይኸው አነሳታለሁ ። በመሃላ አላምንም ። ስሚን ከማንም ጋር ሳነሳ -ስጥልስተፋ -ስዘረጥጥ ነው እምውል ። ይሉኝታ ረስቻለሁ ። ካንተም ጋር ሳነሳት ይኸው ደንታ የለኝ ። (ዳቦውን ይከካና ጠርሙስዋን እንስቶ ጭላጩን ይጎነጫል ።) ተቸርችፋ የለቀች ስሩር ትመስያለሽ ስለምላት ነው የጠመደቺኝ ። ድሮ ኮማሪት ነበር እምትባል ። አሁን ግን ሠልጥናለች ፤ ሴት አዳሪ ነው እምትባል ! ! ሆኖም አላለፈላት ። ያም ሆነ ይኸ እኔ ቸርችፍ ስሩር ነው እምላት ። የገና ስሩር ታውቃለህ ? ጥንግ ነው መሰል እምትሉት ?

ከወይራ ግንድ ተቦርቡራ ፡ ዙሪያዋን ተከርክማ ፡ በቅቤና በሞራ ታሽታ ፡ ፀሐይ ላይና እሳት ዳር እየተለበለበች ከጠጠረች በኋላ ፡ የገና ጥንግ ትሆናለች ። ከዚያ የቡድን አባቶች ይሻኮቱባትና ፡ ሁለቱም ወገኖች ፡ ከባሕር ዛፍ ፤ ከክትክታ ፡ ከብሳና ፡ ከወይራ ፡ ከዝግባ ፡ ከድደሆ . . . . ከግራዋና ከሰንሰልም ቢሆን በተቆረጡ የገና ዱላዎች ፡ በየጐራቸው ተሰልፈው ወደየአጥቂዎቻቸው ግብ የቀሉአታል ። በቅቤና በሞራም ታሽች ፡ ታኮ[illegible]በሙትም ፡ ተሞቀችም ፡ ተለበለበችም ፡ ያው ለመለጋት ብቻ ነው ። እንደገናዎቹ ዱላዎች የቡድን አባትና ጐራ የላትም ። በማናቸውም ግብ ተለግታ መስጠም እንጂ አታማርጥም ። የቡድን አባቶች ከተሻኮቱባት ጊዜ ጀምሮ ፡ ተሰብራ ፡ ተሰነጣጥቃ ፡ ተቸርችፋ ፡ ቆርቁዛ ፡ አልቃ ፡ እስከ ተጣለች ድረስ የገና ዱላዎች ሁሉ መጨዋቻ ሆና ትለጋለች ። አዎን ። ለዚህ ነው እህታችንን የተቸረቸ



ፊች ስሩር እምላት ። (ዳቦዋን ቈርጥሞ ይጨርስና እሶፋው ጫፍ ላይ ይቀመጣል ።) የወንድሜን ሚስት ጠቁማ ወንድ ቤት ያስቀጠረች እሷ ናት ። ወንድሜ ስለሚስቱ አጫውቶህ የለም ? ጉደኛ ናት ። (ዘግየት ብሎ -) ምን ይመስልሃል ?

ዘርፉ

ምኑ ?

ተኮላ

ስለ ወንድሜ ?

ዘርፉ

እ . . . (ዘግየት ብሎ -) ብርቱ መካሪ ያጣ ይመስለኛል ።

ተኮላ

አንተ ብርቱ መካሪ ነህ ?

ዘርፉ

(ዘግየት ብሎ እያቅማማ -) አይ ፡ እንግዲህ እንዴት ብዬ ልወቀው ?

ተኮላ

ሰው መክረህ አሻሽለህ ታውቃለህ ?

ዘርፉ

(እያቅማማ -) አይ ፡ መቸም እንደነገሩ ፤

Scanned by CamScanner

ተኮላ

ሰው መክሮ አሻሽሎህ ያውቃል ?

ዘርፉ

(እያቅማማ -) አይ . . . መቸም እንደነገሩ ፤

ተኮላ

ራስክን መክረኸው ተሻሽለህ ታውቃለህ ?

ዘርፉ

(ዘግየት ብሎ በመጠራጠር አንደበት -) አ - አዎን ። መቸም እንደነገሩ ፤ . . . . . አዎን ፡

ተኮላ

ዳሩ አንተ አለ ጥቁር አፈር ምክር አታቅም ! አለ አፈር ድቤ ምክር አታቅም ! (አጭር ፀጥታ ። ለጊዜው ትንሽ የጸጸት ገጽ ያርፍበታል ፤ ግን ወዲያው ከእንቅልፉ እንደነቃ ይባንንና -) እኔ ግን ራሴን መክሬውም አላውቅ ። ሕ - ሕሊና ከሚሉት ጋር አ - አንግባባም . . . አ - አንጣጣምም ። በ - በውኑም በሕልሜም ከሕሊናዬ እንደሸሸሁ ነኝ ። አዎን አ - አንጣጣምም ። (ወዲያው ከማጀራቱ ላይ ተባይ ይይዛል ። በጣቱ መሃል አሽትሽት አርጎ መሬት ይጥላትና ቆሞ ሁለት ጊዜ



በኃይል በተረከዙ ይረግጣትና ፤ ሦስተኛ አሽትሽት አርጓት ይፈዛል ። እነበረበት ተመልሶ ይቀመጥና ወደ ዘርፉ ዞር ብሎ -) አንተ ከሕሊህና ሸሽተህ ታውቃለህ ?

ዘርፉ

(እያቅማማ -) አይ እንጃ . . . እንጃ . . . ኧረ እኔ እንጃ ።

ተኮላ

(እንደገና ተከገዘ ብሎ ይባንንና -) ለዚህ ይሆናል እኔን ምክር እማያስፈልገኝ ። አዎን ፡ ለዚህ ይሆናል ። (ዘግየት ብሎ -) ምን ይመስልሃል ?

ዘርፉ

ምኑ ? (ሆዱን በስቃይ ደገፍ እንደማረግ ይላል -)

ተኮላ

(ዘግየት ብሎ -) አይ ተወው ። (ዘግየት ብሎ -) ተወው ። (ካጭር ፀጥታ በኋላ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ -) ለወንድሜ ብርቱ መካሪ ያስፈልገዋል አልከኝ ?

ዘርፉ

(በጥርጣሬ -) አ - አዎን ። አዎን . . . . . . ሳያስፈልገው አይቀርም ።

ተኮላ

ነው ። ሳያስፈልገው አይቀርም ። አየህ ፡ ወንድሜ ነገር ሲቀበል የሆያ ውሀ ጣቢ ነው ። ምጥጥ አርጎ ፡ ለጥ - ፀጥ ነው እንጂ ፍልቅም አይለው ። ውሎ አድሮ ትንፍሽም ቢል ነገሩ ሚዛን የላትም ። አንድ አቦሬ የነገር ጉሽ ሽምጥጥ አርጎ ሳያሽረው ጭጭ ነው ። ቢያሽረውም ከሬናፍ ጢስ ብቻ ነው ። (ዘግየት ብሎ -) ትላንት ማታ ፡ ትላንት ማታ አንድ የሌሊት ዘበኛ እጭለማው ጥግ ደገፍ ብሎ ትምባሆዋን በፀጥታ ምጥጥ ጭልጥ ሲያረጋት ፡ የፍሟ ጭላንጭል ግንባሩ ላይ ፈካ ብላ በዝግታ ውድም ስትል አየኋትና ፡ ዘበኛው የእሳት ወላፈን የጠጣ ዓይነት መስሎኝ ነበር ። ወዲያው ከጨለማው ውስጥ ራመድ ብሎ ሲተነፍስ ባየው ጊዜ ፡ (ጮክ ብሎ -) ለካስ አንድ መንጋጋ ሙሉ የኮሾ ሲጋራ ጢስ ብቻ ነበር ! (ዘግየት ብሎ -) የወንድሜም ነገር እንዲሁ ነው ። እሳት ሲጎርስ ውሎ ጢስ ብቻ ነው - እሚተፋው ! (አጭር ፀጥታ ። ከውጭ አንድ ረዥምም ፉጨት ይሰማል ። ተኮላ ጆሮዎቹን አንቅቶ ያዳምጣል ። ወዲያው ሁለት አጫጭር ፉጨት ተከታትሎ ይሰማል ። ተንደርድሮ ሞገስ አልጋ ላይ ይቈምና እራስጌ ያለችውን መስኮት በርግዶ ከፍቶ አንድ ረዥምና ሁለት አጫጭር ፉጨት የታች ከንፈሩን በሁለት ጣቶቹ አጥፎ ካፏጨ በኋላ በፌዝ'ኸት እየተጣራ -)

ሃይ ! ሃይ ! ጋይ ! ሰምቼሻለሁ ! ዛሬ የቁጭራ ቀን ነው አትርሺ ! ጆኒንና በርትን ጥሪና ጠብቂኝ ! ጆኒን ከሪዝ መትቷት ሲጋራ ልትቃርም ባቡር ጣቢያ ወርዳለች ! በርት ደሞ ራስ



ሆቴል ፊት ለፊት የመኪና በር እየከፈተች ሳታጭቅ አትቀርም ! እሷ መቼም ፈረንጅ ሁሉ የሚሰጥ ይመስላታል ! ቲዩሪስቱን ከፒስ - ኮር መለየት አትችልም ! እኔ እንደሆንኩ ዘለዓለም ጠብሻን እንደመታኝ ነኝ ! እዚያው እንገናኛለን ባይ ! ባይ ! (ከሱሪ ኪሱ ውስጥ ሰንጢ መዝዞ መልሶ ይከተዋል ። ካልጋው ዱብ ብሎ ይወርድና -) ዛሬ ቁጭራን ቀይ ቀለም ስንቀባት ነው እምናድር ። ቀይ ! ቀይ ደም ስንቀባት ነው እምናድር !

ዘርፉ

(አሁንም ሆዱን በዝግታ እንደደገፈ ነው -) ምን አልከኝ ?

ተኮላ

(ዝግ ብሎ ብንደት አንደበት -) የቁሽትህ ቁስል ተሻለህ ወይ ?

ዘርፉ

እ ?

ተኮላ

የቁሽትህ ቁስል !

ዘርፉ

(ድንገጥ እንደማለት ብሎ በማቅማማት -) ምን ብ
ሻለኛል ብለህ ነው . . . . .

ተኮላ

(በጩኸት -) ታድያ አትሄድም ! አትሄድም ወይ ነው እምልህ ! (ወደ በሩ ይራመዳል ። ተንደርድሮ ይመለስና የቀዳዳዋን ውታፍ ከጠረጴዛው ላይ ብድግ አርጎ ቀዳዳዋን ይወትፋል ። ተንደርድሮ ውልቅ ይላል ።
(የመድረክ መብራት በፍጥነት ይጨልማል ።)





በማግሥቱ ቅዳሜ ሶስት ሰዓት ነው ። መድረኩ እንደጨለመ ነው ። ካቅራቢያው መሥሪያ ቤት የሶስት ሰዓት የኤሌትሪክ መለከት ይጮሃል ። የተሊላ ሳል ይሰማል ። መብራቱ ሲበራ ቤቱ ባዶውን ነው ። ዘርፉ ወዲያው እየተልጐመጐመና ሆዱን ይዞ እያማጠ ይገባል ።

ዘርፉ

(አልጋውን ደገፍ ብሎ ይቆማል ።)
የጓሮ መውጫም የለው ። መቼም ፊንፊኔ አደባባይ መሀል አይቀመጥ ። . . አይ ከተሜ ! አሁን ይሄ ኑሮ ነው ? ምን አለ መድኀኔ ዓለም እነኚህንስ ልጆች ለአባታቸው ርስት ብታበቃቸው ? አይ ተልከስክሶ ኑሮ ! ዓይነ ጥላ አዙረውባቸው ይሆን ? የጠበል ስምም ሲነሳ ያስገለፍጣቸዋል ። ታናሽየው ማ መላው ሁሉ ለብቻው ነው ። ትላንት በቀትር ተፈናጥሮ የወጣ በደረቀ ሌሊት ቁና ቁና እየተነፈሰ ልቧኩን በደም ነክሮ ተመለሰ ። በእንቅልፍ ልቡ ሲቃዥ ፡ ሲገላበጥ ፡ ሲወራጭ ፡ አርፍዶ ፡ ዶሮ ሳይጮህ ተፈናጥሮ የወጣ እስካሁን አልተመለሰም ። ምን የሚሉ የጭለማ መንገድ ነው በሉ ! እንግዲህ የት ሄደ ይባላል ! የቤቱና የሰዉ ብዛት እንደሁ የከተማ ደን ነው ። የኩሊው ፡ የመኪናው ፡ ያወናባጁ ፡ የየፍርድ ቤቱ ቀጠሮተኛው ፡ የነገረ ፈጁ ፡ የሥራ ፈቱ ፡ የለማኙ ፡ የወፈፌው ፡ ምኑ ጉዱ ! ኹልቈ መሳፍርት አደል እንዴ ! ምን አለ የነኝህን ልጆች እግር ወደ አባታቸው ርስት ብትመራልኝ ? እኔንማ ተወኝ ብልህ ጨከንክብኝ ። ወይ እንድያህን ጠርተህ አልወሰድከኝ ። (የተሊላ ሳል ይሰ

ማል ፤ ወዲያው ጮክ ብሎ -) እንደምን አረፈዳችሁ እዚያ ቤቶች ! አልሰሙኝም መሰለኝ ። (የተወተፈውን ቀዳዳ ከፍቶ ጮክ ይልና -) ደህናም አላረፈዳችሁ ወይ ! እግዚአብሔር ይማርዎ ! . . . . አይ ! አልሰሙኝም መሰለኝ ። (ውታፉን ጠረጴዛ ላይ ይተዋል ። ሞገስ በብብቱ ሥር በጋዜጣ ወረቀት የተጠቀለለ መናኛ ፉርኖና በቀኝ እጁ ፖሊስና እርምጃው የሚሰኘውን ጋዜጣ ይዞ ይገባል ። ፊቱ በሀዘን ተላብሷል ። ዳቦውን ጠረጴዛው ላይ ይጥልና አልጋው ላይ ይገነደሳል ። ዘርፉ ወደ ሞገስ እየሄደ -) እንኳን መጣህ ሞገሴ ፤ እንኳን መጣህ ። እማዋይህ ስሞታ አለኝ ። አየህ ሞገሴ ፤ (ሞገስ ግን የአእምሮው ፀጥታ መረበሽ በግምባሩ ላይ ቢነበብም ዘርፉ አላወቀለትም ። ከተጋደመበት ቀና ብሎ ጋዜጣውን እንደጨበጠ ቁጭ ይላል ። ዘርፉ እያቅማማ ይቀጥላል -)

አየህ ሞገሴ ፤ መቸም የእግዚአብሔርም ቃል «አክብር አባከ ወእምከ» ነው እሚል ። (ያቅማማል -) አየህ ሞገሴ ፤ አባት ልጁን ታላቅ ታናሹን ነው እሚመክር ። አንተም እንድትመክርልኝ ነዋ ። መቸም ባልወልዳችሁም አባታችሁ ነኝ ። «የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ» ነው ከነተረቱ ። ወንድምህ ግን እንደምታየው መላው ሁሉ ሌላ ነው ። ቄሀ መጣ ሳይባል በነገረ ቀደም ዱብ ዕዳውን ይወርድብኛል ። መላ ሁናቴው አቅል የለው ። አይ ፣ የለም ሞገሴ ፤ አልሆነኝም ። ብታስታግስልኝ ይሻላል ። ቀናውን ነገር ሸብረክ አርጎ ቱግ የሚያሰኝ ቆሌ አለው ። በጤና አገር ቱግ ብሎ ግሥላ ነኝ



ይላል ። አልፎ ተርፎ ደሞ «ሂድ» የሚሉ አማርኛ አለው ። እንዲያው እኮ ደርሶ «ሂድ - ሂድ !» ያሰኘዋል ። አሁን ይኸ አማርኛ ነው በል ? እስቲ እግዜር ያሳይህ ፥ ይኸ አማርኛ ነው ? አይ አይሆንም ሞገሴ ፤ አስታግስልኝ ። (ሞገስ ጋዜጣውን ትግ ብሎ በጸጥታ ደጋግሞ እያገላበጠ ከቶ አላዳመጠውም ። ዘርፉ ዘግየት ብሎ አልጋው ራስጌ ያለችውን ጩቤ ከሩቅ እያመለከተ ግልፍ እንዳለው ዓይነት -) ያቺን ጩቤ አየህልኝ ! ያቺን ጩቤ አየሃት ሞገሴ ! እኔ አባትህ ሥ[illegible]ታለሁ ። ልጅ አይኑረኝ እንጂ እሷ ልጄ ናት ። ቀኝ እጄ የክፉ ቀን አይዞህ ባዬ ናት ። በሰላም ጊዜ ከራስጌዬ ፤ በስደት ጊዜ ከሽንጤ አትለየኝም ። ወዳጅ ዘመድ ቢከዳኝ እሷ አትከዳኝም ። አብራኝ ናት ፤ አንድዬ ናት ። አይዞህ ትለኛለች ! ታሞካሸኛለች ። ስሞታዬን ታደምጣለች ። ዋይታዬን ትበቀላለች ። አየህ ሞገሴ ፤ እኔ አባትህ ሠርቼባታለሁ !

(ሞገስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጋዜጣው ላይ ከመተከዝ ነቅቶ ዘርፉን እንደመፍዘዝም ፥ እንደግራ መጋባትም ፥ እንደትዕዝብትም ትክ ብሎ ይመለከተዋል ። ያጠናዋል ፤ ይገምተዋል ። ዓይን ለዓይን ትክ ብለው ለአጭር ጊዜ ይተያያሉ ። የዘርፉ ዓይን በለዘብታ ቀለስ ይላል ። ሆዱን ደገፍ እንደማረግ አርጎ ወደ አልጋው ይሄድና አንገቱን ደፋ አርጎ ይቀመጣል። ረዥም ፀጥታ ።)

Scanned by CamScanner

ሞገስ

(ፊቱን መጀመሪያ ወደ ጋዜጣው ዳግመኛ ወደ ዘርፉ መለስ አርጐ በጸጸት እንደበት -) አብዬ ፡ ይኸ ጋዜጣ ያረዳኝን መርዶ ላርዳህ ?

ዘርፉ

(ደንገጥ ብሎ -) የምን መርዶ በል !

ሞገስ

ፖ -) ስማ ! (የነባል -)
ሀት ወንበዴዎች ፡ ትላንት ዓርብ ከምሽቱ አራት ሰዓት ሩብ ላይ ቁጭራ ተብሎ ከሚታወቀው ሠፈር በስተግርጌ ከሚገኘው ድልድይ በስተምዕራብ ሠላሳ ሜትር ገባ ብሎ በሚገኘው ፡ ልዩ መጠሪያው ያበጋዝ ጠለለው መንደር ከሚሰኘው አካባቢ ፡ ለጊዜው ልዩ ምልክታቸውና ቁመናቸው እንጂ ስማቸውና አድራሻቸው ያልታወቀ ሦስት ወንበዴዎች ፡ አቶ አሻግሬ ጉርሙ ከተባሉት ሰውዬ ቤት ፡ ቅጥር ግቢውን ሰብረው ገብተው ፡ አቶ አሻግሬን ታፋቸው ላይ በጩቤ ወግተው ፡ ትሁኔ የምትባል ገረዳቸውን አስፈራርተው እንዳመለጡ ፡ ከሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ የተገኘው ወሬ ገልጾአል ። አቶ አሻግሬ የወንበዴዎቹን ስምና መልክ ካሁን ቀደም ፈጽመው አለማወቃቸውን አስረዱ ። ገረዳቸው ወይዘሮ ትሁኔ ግን ፡ ከሦስቱ አንደኛው የቀድሞ ባሌን ታናሽ ወንድም ተከላ ይጥናን ይመስለኛል ፡ ሆኖም ቀድመው በጥፊ ቢመቱኝ ጭው ብሎብኝ ስለነበረ እርግጠኛ አይደለሁም፡



የቀሩትን ሁለቱን ግን አላውቃቸውም ስትል ቃሏን አስመዘገበች ። የቀድሞ ባሏን መኖሪያ ቤት ለፖሊስ እንድትመራ ብትጠየቅ ፡ ከተለያዩ ከሁለት ዓመት የበለጣቸው መሆኑንና ፡ የድሮውን እንጂ አሁን ያለበትን ሠፈር አላውቀውም አለች ። ይሁንና እህቱ ቁጭራ ሠፈር በሴት አዳሪነት መጠጥ የምትነግድ መሆኗንና ፡ የሷን ቤት ማወቋን ፡ የቀድሞ ባልዋና አሳዳሪዋ አቶ አሻግሬም አንድ መሥሪያ ቤት መሥራታቸውንም ስለገለጸች ፡ ጉዳዩን የሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ በመከታተል ላይ መሆኑን አስተላልፎልናል ። አቶ አሻግሬም ለጊዜው በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በሕክምና ላይ ናቸው ።»

(አጭር ፀጥታ ። ጋዜጣውን አልጋው ላይ ወርወር አርጐ ጥቂት ከዘገየ በኋላ በውይይት እንደበት -) ይኸውልህ ፡ ጠዋት አገር ጤና ነው ብዬ ወደ ቢሮ ስገባ ፡ ፖሊሶች ይጠባበቁኝ ኖሮ ፡ ና ለምርመራ ትፈለጋለህ ብለው ይዘውኝ ሄደው ስመረመር ዋልኩ ። ተከላም ቤት እንደመጣ ፡ ወይም ያለበትን እንዳወቅሁ ለፖሊስ እንዳስታውቅ ቃል ገብቼ ፡ ዋስ ጠርቼ ተለቀቅሁ እልሃለሁ ።
(ረዥም ፀጥታ ።)

ዘርፉ

(በሀዘን ያማርራል -) አዬ ! አዬ እመብርሃን ! አዬ ! (አጭር ፀጥታ ። -) ታድያን አሁን ምን ይበጃል ሞገሴ ? (አጭር ፀጥታ ።-) ተከላ ድንገት ይገባል ። በድንጋጤ ያዩታል ። ተከላ ቤት ውስጥ ሌላ ሰው እንዳለ መልክት ይልና ወደ

በሩ መለስ ብሎ ደጅ ደጁን ከተመለከተ በኋላ በሩን ከውስጥ
ይቀረቅረውና እጆቹን ሱሪ ኪሶቹ ውስጥ ከትቶ እየተቁነጠነ
ጠ ይቆማል።)

ተኮላ

(ለመጀመሪያ ጊዜ ለዘብ ባለ አንደበት -) አብዬ ፤ . .አብዬ ፤
አ - አባታችን አ - አባቴ ምን ይመስል ነበረ ? (አጭር ፀ
ጥታ ።)

ዘርፉ

አባትህማ ፣ . . . አባትህማ ፡ አገር የመሰከረለት ጀግና ነበረ
ተኮላዬ ። ሲተኩስ የማይስት ፣ ሲቆጣ የሚደመጥ ፣ ሲታ
ጠቅ የሚፈራ ነበር አባትህ ። ወንድ ነበር አባትህ !

ተኮላ

(ተንገፍግፎ -) ተወው ፡ ተወው ። (ዘግየት ብሎ -) ተወው።
(ካጭር ፀጥታ በኋላ -) አየህ ፣ እኔናአንተ ስለማንግባባ አን
ጣጣምም ። አባቴ ምን ይመስል ነበር ስልህ ፡ ቁጣውን
ሳይሆን ሳቁን ነው ። ሲታጠቅ ማስፈራቱን ሳይሆን ሲለ
ብስ አማማሩን ነው ። ሲተኩስ ማነጣጠሩን ሳይሆን ሲጫ
ወት ሲስቅና ሲያወጋ ለዛውን ነው ። አንተ የምትነግረኝ
የፈለግኸውን እንጂ የጠየቅሁትን አይደለም ። እኔ ላውቅ
የፈለግሁት ፡ አባቴ ሲያዝን ትካዜው ፡ ሲስቅ ፍንጭቱ ፡
ሲጫወት ለዛው ፡ እንዴት እንደነበረ ነው። የላዩን ሳይሆን
የውስጡን የልቡን ነው ። «ወንዱን» አባቴን ሳይሆን ሰውዬ
ውን አባቴን ነው ። «ጀግናውን» አባቴን ሳይሆን ወላጅ አባ



ቴን ነው ፤ (ዘግየት ብሎ -) ገባህ ? ? (ዘርፉ በነገሩ ተወና
ብዶ ፀጥ ይላል - ተኮላ ዘግየት ብሎ ተስፋ በቆረጠ አንደ
በት) ተወው ፤ . . . . . . ተወው ! ! (አጭር ፀጥታ ።)

ዘርፉ

(ካልጋው ራስጌ የወደቀችውን ትንሽ ከዘራ አንስቶ ይወ
ስዳትና አጠገቡ ያጋድማታል ። -) እያት ይቺን የቀርከሃ
ምርኩዝ ሞገሴ ። አያታችን ናቸው ለአባታችሁ የሰጡት ።
በአያታችን ጊዜ ገድሎ ያልተቀባ አያገባምና፡ ዝሆን አደን
ሄደው ነው ከበረሃ የቆረጧት ። ታዲያን አባትህ ቅዳሚ
ትና ሰንበት ከእጁ ለይቷት አያቅም ። ቤተክርስቲያን ለመ
ሳም ሲሄድ ፡ አደባባይ ለነገር ሲሄድ ፡ በየሸንጎው ለእርቅ
ሲሄድ ፡ ይቺን ተመርኩዞ ነው ። ደህና ሽመል ሞልቶ ምን
ይዘሃት ትዞራለህ ሲሉት ፡ «የኋሊት ላስተውልባት» ብዬ ይ
ላል ። «የኋሊት አላስተውል ያለ የነገ መድረሻው አይጠበ
ቅምና» ይል ነበር ። (ትንሽ ዘግየት ብሎ ምርኩዝዋን ሲያነ
ሳት ጎንበስ ሲል ሆዱን በስቃይ ደግፎ ፣ ተንበርክኮ ይቀራል።
ሞገስ በዝግታ እዚያው ሲያስቀምጠው ተንፈስ ይልና እያቃ
ሰተ ይቀጥላል ።)
እየህ ሞገሴ ፡ የነገሬን መጣምና አለመጣም ሳይሆን እኔም
የማውቀውን ነው ። ያባታችሁ «ሳቁና ጨዋታው» ሳይሆን
ቆራጥ ወንድነቱና ብርቱ ገበሬነቱ ነው እሚታወሰኝ ።
(ዘግየት ብሎ በስቃይ እያማጠ መዳፎቹን ወለሉ ላይ ፊት
ለፊቱ ዘርግቶ ልቅሶ ባነቀው አንደበት) ይህን እጄን አያችሁ

Scanned by CamScanner

ልኝ ? ? . - ይህን እጄን አየችሁልኝ ? ? ጥቁር አፈር ሲገፋ ኖር አፈር መስሎአል ። ከበሬና ከወይፈን ጋር ሲተሻሽ ከርሞ ጠረኑ የከብት ነው ። በክረምት ከእህል ጋር ታርሶ ፡ ተጎልጉሎ ፡ ታርሞ ፡ በቢጋ ደሞ በንዳድ ሃሩር ደርቆ እንደ ጫራ መስኖ ተሰንጥቋል ። ቢሆንም ይህ እጄ ያያቶቼ ጥቁር አፈር እሳዳጊ አባቱና መተማመኛ ቤቱ መሆኑንም ያውቃል ። እጄ ፡ አዝመራው ሲያብበለት እንደባለሞያ ሴት ወጭት ይወዛል ። መከሩን ንዳድ ሲመታው እንደንፋጣ ኮረት ያክካል ። ሆነም ቀረ ፡ እጄ በዘመኑ አማፍሮኝ አያውቅም ። አሁን ግን ቀኑ መሽቶበታል ሞገሴ ። የሰድሜው ጀንበር ወደመጥለቋ ናት ። ከእንግዲህ ቢያርፍም ፡ ያባታችሁን እርስት ጫካ ባስወረረው ፡ አፈር በማይነካው እጃችሁ እንጂ የኔማ እጅ የዘመን ግብሩን አከናወነ ። ሞገሴ ፡ . . . . . . (ብሎ ይጀምርና ተስፋ በመቁረጥ ይተወዋል ። አጭር ፀጥታ ። ሞገስና ተኮላ ይታያዩና ፊታቸውን ይመልሳሉ ። ወዲያው ዘርፉ ሆዱን በስቃይ ጨብጦ ያምጣል ። የተሊላ ሳል ይሰማል ።)

ተኮላ

(የተሊላ ሳል እንዳለቀ በመበሻቀጥ እንደበት -) እንዴ እ ምጦ ሲያበቃ ሌላው የነቀርሳ ሳሉን ያንፈቀፍቃል ። (ዘግየት ብሎ - እንደልማዱ ዞር መለስ በማለት በፌዝ አንደበት ያነበንባል) አሣዘንከህ አብዬ ? ማሣዘን ሰጣዬ ነው ። (ዘርፉ የታፈነ ልቅሶ ስርቅ - ይለዋል ።) ተኮላ ዘግየት ብሎ ይቀጥላል ።) አምስተኛ ክፍል ሆኜ ማስፈራራዬ እም ትመስል ፡ አንዲት አስቀያሚ ልጅ ፡ እምባ ምንድነው አለች። «በሉ ምንድነው ?» አለች ። «እኔ ራሴን ካወቅሁት ፡ በግም ባሬ ላብ እንጂ ፡ ባይኔ እምባ አይወጣም» አለች ። «ጨክኖም የመጣ ቀን ፡ ልቤን ይጭነቀው እንጂ ፡ ሁሉን ሆድ ይፍጀው እንጂ ፡ አይኔ ፍንክችም አይል ፡ እምባ ምንድነው» አለች ። (ዘግየት ብሎ) ታዲያ አሁን ሰው ሆናለች ፤ ዛሬ ራሷን ችላ ለች ፤ እምባ አሚወጣቸውን ፡ ልቅሶ ያሸነፋቸውን ፤ ቀጥራ እያከራየች ፤ . . . . . አዎን ራሷን ችላለች ፤ . . . ዛሬማ ሰው ሆናለች ። (ዘግየት ብሎ በመሰ) እያገለፈጠ ወደዘርፉ ይጠጋል -) እና አንተም አታልቅስ ፡ ግድየለም አትንፈቅ ፈቅ ፡ . . . ማለት አብዬ ዘርፉ ፡ አሣዝኜህ እንደሆን ፡ ማሣ ዘን ሰጣዬ ነው ። . . . አየህ አብዬ ዘርፉ . . . . .

ሞገስ

(ድንገት በንዴት ብድግ ብሎ ዞር ይልበትና ጋዜጣውን እያሣየው በጩኸት -) እሱን ተወውና ይህን ጋዜጣ አይተ ኸዋል ! ! ? - (ያፈጥበታል ። ተኮላ ፀጥ ብሎ ይመለከተ ዋል ። ከአጭር ፀጥታ በኋላ ሞገስ ንዴቱ ቀዝቀዝ ይልለትና ሥፍራው ተመልሶ እንደተቀመጠ በለዘበ አንደበት -) እሱን ተወውና ይህን ጋዜጣ አይተኸዋል ? . - (አጭር ፀጥታ ።)

ተኮላ

(ነገሩ ገብቶት እንዳልገባው በማስመሰል እንደዋዛ -) ማንን ነው እምተወው ? አብዬ ነው እምባውን ? (አጭር ፀጥታ ። የሴር መንፈሱ እያደረ ሲያጥለቀልቀው በትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ፡ በዓይኖቹ መቃገርትና በመቁነጠነቁ ይታወቃል ። ወዲያው ወደ ዘርፉ መለስ ብሎ -) አብዬን እንደሆን ፡ ከመተውም አልፌ ፡ ብርድ ልብሴን ሰጥቼ ፡ ሲጠራኝ አቤት እያልኩ ፡ ሲልከኝ ወዴት እያልኩ ፡ ደስ እንዳሰኘሁት ነኝ ። ከዚህ ወዲያ ምን ልፍጠር ? እስቲ እንግዲህ ፍረዱኝ ? ነጋ ጠባ ቆሽትህን ፡ ተሻለህ ወይ ? - እላለሁ ። ቁመናውን አይቼ ፡ ደም ግባቱን አይቼ ፡ እግዚኦ የኔው ሰዳ ፡ የኔው ጉድ ነህ እላለሁ ። ማልጄ እየመጣሁ ፡ እግዚኦ አበስኩ ገበርኩ ፡ ለካስ የኔው ፈተና ፡ እግዚኦ የኔው ፍርጃ ፡ አብዬ ነህ ፡ እላለሁ። ሌላ ምን እፈጥራለሁ ! ፍጥጥ ብዬ እያየሁ ፡ የኔው ጉድ ነህ ! እላለሁ ። (ዘርፉ የሕመሙ ስቃይ ሲበዛበት ሆዱን በሁለት እጆቹ እየደገፈ ያምጣል ። ሞገስ ደግፎ ይወስድና ራሱ መኝታ ላይ አስቀምጦ ጋደም ሲያደርገው ተኮላ በዓይኑ እየተከተለ -) ከዚያ ወዲያ ምን ላድርግ ? - ከዚህ ወዲያ ምን ልፍጠር ? ! (ረዥም ፀጥታ ።)

ሞገስ

(ዘርፉን አስደግፎ ካስቀመጠ በኋላ የተናነቀውን የንዴት ሲቃ የግድ አፍኖ እየያዘ ተኮላን ቀረብ ይለውና -) እባክህን ጥያቄዬን መልስልኝ ተኮላ ? ? ይህን ጋዜጣ አይተኸ



ዋል ነወይ የምልህ ! !

ተኮላ

(በምሬት እያከታተለ -) አዎን ብልህ ምን ታተርፋለህ ? ? አዎን ብልህ ምን ታተርፋለህ ? - አዎን ብልህ ምን ታተርፋለህ ? ! ! (ወደ መድረኩ በስተቀኝ አፈንግጦ ይወርድና በንዴት እንደበት -) አየህ ወንድሜ ፡ የዚህ ሁሉ ሳቢያ አንተ ነህ ! ! (ሞገስ ደንግጦ ሲቆም በማረጋገጥ አንደበት እያፋጠነ ።-) አየህ ወንድሜ ፡ አንተ እንቆቅልሽ ነህ ! ! አዎን ! የፌዝ ተረት ነህ ! ! ፀሐይ ስትወጣ ተጀምረህ ሌሊት እንቅልፍ እስኪጥል የምትተች ቀልድ ነህ ! ! በመንደር ለጎረቤቶችህ ፡ በቢሮ ለጓደኞችህ ፡ የቡና ማንቃረሪያ ትኩስ ወሬ ነህ ! ባደባባዩና በድፍን ከተማው ከዳር እስከዳር የምታስተጋባ ፌዝ ነህ ! አዎን ! ! አዎን ! የምትወራ ፡ የምትደመጥ ፡ የምትተች ፡ ቀልድ ነህ ! (ሞገስ በንዴት ተንደርድሮ ይመጣና በጥፊ ይመታዋል ። ተኮላ ለጊዜው እሚሆነው ጠፍቶት እንደበድን ፀጥ ይላል ። ሞገስ ንዴቱ በረድ ብሎለት እንደመፀፀት እየቃተው ወደሶፋው ሄዶ ጫፉ ላይ አንገቱን ደፋ አድርጎ ቁጭ ይላል ። በሃዘን ኩርምት ይላል ። ይተክዛል ። ተኮላ ሞገስን እያስተዋለ የፌዝ ፡ የመስሪ የእልህ ሲቃ በተመሳቀለበት አንደበት እንደመሣቅ ይቃጣውና ወዲያው ምሬት በዋጠው ሲቃ ተርገፍግፎ ይንሰቀሰቃል ። ከደጅ የከባድ ጫማ ኮቴ ሲሯሯጥ ይሰማል ። ተኮላ ብርግግ ብሎ በሩን ከፈት ያደርግና ወደ ደጅ መልከት ብሎ በድን

ጋጤ መለስ ይላል ። የፖሊስ ፊሽካ በብዛት ተከታትሎ
ይሰማል ። ሞገስና ዘርፉም ደንግጠው ፀጥ ይላሉ ። ተከላ
በሩጫ ተንደርድሮ ወደ ተመልካቹ ሕዝብ መሃል ሲሾሽ የመ
ድረክ መብራት ደብዘዝ ብሎ ያዳራሹ ይበራል ። በሕዝቡ
መሃል ሁለት ፖሊሶች ይዘውት ሲወጡ የመድረኩም ያዳ
ራሹም መብራት በፍጥነት ይጨልማል ።)



“ ለ ”

በሰባተኛው ቀን ፣ ጧት ፣ ለሶስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ነው ። የእግረኞች ጫጫታ ፣ የጫማ ፣ የመኪናዎች ሞተርና ጡሩምባ እንደመትሮው ይሰማል ፣ ዘርፉ ተኝቷል ።)

ሞገስ

(ካልጋው ላይ ተነስቶ ፣ ከኮቱና ከግራ እግሩ ጫማ በስተቀር ልብሱን ለብሶ ፣ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጦ ፀጉሩን ሲያበጥር መብራት ይበራል ። ፀጉሩን ሲያበጥር ኮቱንና ጫማውን ሲያጠልቅ ፣ ተስፋው በገበረ የንዝሕላልነት ሁናቴ ነው ። አልፎ - አልፎ ቀልቡ በትካዜ ስልብ ይልና የሚያደርገውን ይተወዋል ። እጁና እግሩ ቢያንቀሳውስም በዘልማድ ነው ። ሰዓቱን ዓየት አርጎ በስጋት ብድግ ይልና ወዲያው ደግሞ ተኮላ በየቦታው ከበታተናቸው የሲጋራ ቁርጥራጮች አንደኛውን ሲያይ ቆም ይልና በዝግታ ከወለሉ ላይ ብድግ ያደርጋታል ። ለጥፍር መቆንጠጫ ብቻ የተረፈች አመድዋ ከጠቅላላ መጠኗ የበለጠ ፣ ማጣሪያ የሌላት ብጣቂ ናት ። እንደያዛት በትካዜ ይዋጥና አላጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ ይፈዛል ። እንደፈዘዘ በባከነ ቀልቡ እሽትሽት አርጎ አመዷን ሲያበናት ተበጣጥቃ ትወድቃለች ። የቦነነውንና የተበጣጠቀውን እራፊ ትክዝ ብሎ እያሽቶ የለ ከገዛ ሕሊናው እንደሚወያይ ሰው ያነበንባል ።) . . . . . በዚች በሰባት ቀን ውስጥ ሁለንተናው ተቀየረ ድሮ ተኮላ ሲሉት ቱግ የሚለው ትላንት ወህኒ ቤት አንገቱን ደፍቶ «ጋሼ» አለኝ ። በሰባት ቀኑ ፣ የሃያ ሶስት ዓመት ጎልማሳነቱ ቀዝቅዞ ፣ የዘጠና ዘመን ሽማግሌ ሆነ ። ውሃ ቀጠነ ብሎ ደም



ያግት የነበረው ዓይኑ ፣ ዛሬ እንደመርፌ ቀጥኖ ልቦናውን በምርምር እሚጠቅም ይመስላል ። አንዳች ነገር ከመተንፈሱ በፊት ደጋግሞ - አሠልሶ ያሰላስላል ። «ጋሼ» አለኝ ። «ያባት እርግማን አለብን ወይ ?» አለኝ ። የምሰጠው መልስ ጠፍቶኝ ሕሊናዬ ተሳከረ ። መከራ ስትመክረን እኮ በጭካኔ ነው አልኩት ። (ዘግየት ብሎ -) ሰሞኑን ሕልሜ ተቀይሯል አለኝ ። ወደ ውስጥ እንጂ ወደ ውጭ አላልምም ይላል ። ባኮርፍ ፣ ብቆጣና ብጠላም ፣ ከእኔነቴ ብቻ ጋር ነው አለ ። ለካስ የሚያኮርፉትን ማጣትም ዓለምን መነፈግ ኖሯል ቢለኝ ፣ እኔንም ግራ ገባኝ ። (ዘግየት ብሎ -) ተከዝ ብሎ ቀና ሲል ደም ሥሩ በግምባሩ ላይ እንደትኩስ ሰምበር ይጠመጠምበታል ። አተኩሮ ሲመለከት ፣ የዓይኑ ብሌን እንደወስፈንጥር ሾሎ በጣራ ሽንቁር እንደጠለቀች የገና ጨረር አናት ቀዶ የገባ ይመስላል ። በግርግር ዓለም በተንኮል ተወናብዶ የጠጠረው ወንድሜ ፣ በመከራ ቤት በሰለ ። ከምን መጣህብኝ እንጂ ፣ እንኳ መጣህልኝ ብሎኝ የማያውቀው ተኮላ ፣ አንገቱን ቀልሶ «ጋሼ» አለኝ ። ወትሮ ላይ ላዩን በተንኮል ጠጥሮ ፣ ውስጡ ነቅዞ ይታይ የነበረ ልቦናው ፣ ትላንት ውስጡ በስሎ ላዩ በመከራ ቆስሎ ያየሁት መሰለኝ ። ልጅነት አባክኖ ያሰከረው ተኮላ ፣ ትላን… ዕድሜ ያስተማረው መካሪ ሽማግሌ መሰለኝ ። ተለውጧል ። የሰው አለኝታ እንዲያ ሸሽቶት የነበር ወንድሜ . . . (ካካራቢያው መሥሪያ ቤት የሶስት ሰዓት መለከት ሲነፋ በርግጎ ይነሳና ለመውጣት ራመድ ብሎ ዘርፉ ራስጌ ቁጭ ይልና ፣) . . . አብዬ ፣

አብዬ ተነስ እባክህ ፡ ትንሽ እህል ቅመስ ፡ ባይሆን እንኳ ውሃ ተጉመጥመጥ ! (የውሃውን ጠርሙስና ጠረጴዛው ላይ በወረቀት ተጠቅልሎ የተቀመጠውን የተገመሰ ዳቦ ዘርፉ መኝታ ግርጌ እያስቀመጠ -) አይዞህ ቀና በል ፡ ከተኛህ በትማ ይተኛብሃል ። ዛሬስ ከየትም ተብድሬ ቢሆን ፡ መድኃኒትክን ሣልገዛልህ አልመጣም ። (እየቀሰቀሰው -) እኮ በል አይዞህ ። (ዘርፉ እያቃሰተ ቀና ሲል ሞገስ በችኮላ ይወጣል ።)

ዘርፉ

(ሕመሙ ከወትሮ ይበልጥ ተጫጭኖታል ። እንደምንም ተጣጥሮ ቀና ሲል በጸሎቱም ፡ በትችቱም ፡ ትንፋሹ ቁርጥ - ቁርጥ ይልበታል'።) አንተ ታውቃለህ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ አንተ ታውቃለህ ፡ - (በትችት አንደበት -) እኔማ ብለምንህ የተዋረድ አታካሮ ገጠምከኝ ። ውሰደኝ እምቢ ፡ ተወኝ እምቢ ፡ ፍንክች - ያባ-ቢላዋ-ልጅ ። አሁንስ ጃጀህ መሰለኝ የማርያም ልጅ ። ምንቸቷ እንደማይሰማላት ባልቴት እኝኝ ብቻ ሆኖ ይቅር የኔና ያንተ ነገር ። አንቺስ ምናለ ተው ብት ይው እመብርሃን ? ? - እነኚህንም ልጆች ለአባታቸው እርስት አብቃልኝ ብለው ፡ አንዱን ለቁም ስቅል ፡ አንዱን ላወህኒ ቤት ዳርጎ ዝም አለኝ ። (በሕመም እያቃሰተ ዘማ የት ይልና በፀሎት አንደበት -) ወልደ አብ ተለመነኝ ፡ ወልደ ማርያም ተለመነን ፡ እግዚአ ተለመነን ፡ ሰማይን አለባላ ፡ ምድርን አካስማ የዘረጋህ ጌታ ፡ አንተ ታውቃለህ ።



አንተ ታውቃለህ ። (እንደማዘጋት ይልና በሕመም አቋርጦ ድንዝዝ ይላል ።) ተው አላልቅስብህ ተው ፡ ተው አላማር ርብህ ተው ፡ ሲሆን ቶሎ ለንስሃ ሞት አብቃኝ ፡ ባይሆንም ተወኝ ፡ ተው የማርያም ልጅ ተው ። ተው እናቴ ተው . . . እነኚህንም ልጆች ካባታቸው እርስት አታሸሽ ፡ በቃህ ። ከጥቁር አፈር አታሸሽ ፡ በቃህ ። ያንንም ከወህኒ ቤት ፡ ይኸ ንንም ከቁም ስቅል አውጥተህ ወደአባታቸው ርስት ምራ ቸው ። የአዝመራን ፡ የመከርን ፡ የጥቁር አፈርን ጣዕም አሣያ ቸው ። . . . እንዴት አደራችሁ እዚያ . . (ድምፁን ከፍ አርጎ ሰላምታ ሊጠይቅ ሲል በሕመም አቋርጦ ድንዝዝ ይላል ። ወዲያው ትንፋሹ ትንሽ መለስ ሲልለት በስቃይ እያቃ ሰተ ። -)

ድንግል መሬት ብላኝ ስትል ፡ በግምባር ወዝ ጥረህ ግረህ ፡
ማኅፀኗ ተከፍቶ ሣለ ፡ ዘር ከልክለህ ፡ ለአረም ዳርገህ ፡
ኸረ የጥቁር አፈር ያለህ ! ያዝመራ የመከር ያለህ !
ምድር ያለዘር ተትቶ ፡ ማሣ ያለርሻ ተረስቶ ፡
ንዳዱን ዝናብ አርሶት ፡ ወዙን ፀሐይ አቅለጥልጦት ፡
ፍሬውን አረም አፍኖት . . . .
ነፍሴ እያለች እንዴት ይምከን ፡ ሣልበቃ ለንስሃ ሞት?
አውድማው አቤት እያለ ፡ ሞፈር የሚይዝ ከየት ይምጣ ?
ከግጦሽ የሚመለስ ከብት ፡ ኸረ እንዴት ተቀባይ ይምጣ ?

Scanned by CamScanner

ማን ሊከፍትለት ነው ጋጣ ?
ጮጮውን ማን ይዞ ይውጣ ?
ቀየው ለአራዊት ሲሰጣ !
ያባት እርስት መና ስትሆን ፤ ሞፈር የሚያነሳው ሲያጣ !
አፈር የሚጭረው ሲያጣ !
ወይ አንቺ የእርግማን ዕጣ ! !
እንደምድረ በዳ አዞራት ፡ አውድማ እሚረግጠው ሲያጣ ! ! . . . .
ወይ አታምጣ ! ! ወይ አታምጣ ! ! ! !
(በሕመም ተይዞ ዘግየት ይላል ።)
እራስ ትናጋው እስከሚያር ፤ ምን መርሮት ያለቅሳል ቢሉ ፤
ከመወለዱ ታይቶት ነው ፡ ይላሉ ጥቁር ዕድሉ . . . .
ተረት ሆኜ መቅረቴ ነው ፡ ለፍሬ ዕድሜዬ ሳትበቃ ፤
ምኞቴ እንደጉም መጥቃ ፡
ተስፋዬ እንደጉድፍ ወድቃ ፤
የወንድሜን ልጆች ጭምር ፡ ለርስታቸው ሳላበቃ !
(በሕመም ተይዞ ዘግየት ይላል ፡) ወዲያው ትንፋሹ መለስ ሲል በጣም በደቀቀ ድምፅ ፡ በዘለሰኛ ስልት ያንጎራጉራል ። ከስልቱ በቀር ቃሉ ከድካሙ የተነሳ አልፎ-አልፎ ብቻ ነው እሚሰማው ።)



አፈር ብመስል እንኳን እንኳን . . . . .
ሟቹ አለኝ ጓዴ ፤ ሟቹ አለኝ . . . . . .
አፈር መስዬ ቢያየኝ . . . . .
አፈር ብመስል ምን ከፋኝ
ፈጥራ መግባ ልትበላኝ . . . . . . .
አፈር ብመስል እንኳን እንኳን . . . . . .

(እያንጎረጎረ ፡ ሞገስ አልጋ ላይ ያስቀመጠለትን ዳቦ ያዝ ያረግና የውሃውን ጠርሙስር ለመያዝ ቀና ሲያደርገው ፤ ያመልጠውና ወድቆ አልጋ ስር እየፈሰሰ ይንከባለላል ። ተስፋ በመቁረጥ መለስ ብሎ እንጉርጉሮውን ለመቀጠል ሲል ፡ እያደር ወደማቃሰት ስልት ይቃጣል ። እያማጠና እያቃሰተ መልጎምጎሙ ለዘብ ሲል ፡ ሞገስ አንድ ጽሑፍ የሰፈረበት አሮጌ ሉክ ወረቀት ከተቀደደ አንቬሎፕ ጋር አንከርፍፎ ፡ እንደዋዛ በትካዜ ይገባና ፡ አልፎ ራሱ መኝታ ጫፍ ላይ ደገፍ ብሎ ይቆያል ።)

ሞገስ

(ወዲያው ፈገግ እንደማለት ብሎ መጠነኛ ፍሥሐና ትካዜ በተመሳቀለበት አንደበት ወደ ዘርፉ መለስ ይልና -) አብዬ፡ ተ - ተኩላ ከወህኒ ቤት የላከልኝን ደብዳቤ አየኸው ? . . ላንብልህ ነው ቸኩዬ የመጣሁት ። ይኸውልህ ። እንዲህ ይላል ። «ለአጎቴ ለአብዬ ዘርፉና ለወንድሜ ሊጋሼ ሞገስ ይጥና . . . እንደምን ከረማችሁ ? አብዬ ተሻለው ? - እኔ ደህና ነኝ ። እውነቴን ነው ሙት ፤ . . . ደህና ነኝ ። አየህ ፡ እዚህ አብሬአ

ቸው የታሰርኩት ሁሉ ፣ ገበናቸው እንደኔው በአደባባይ ተተ ንትኖ የተጋለጡ ናቸውና ፣ አይገበዙም ። አንዱ የሌላውን ቱስል በይፋ ያያል ። ሌባው እንዴት እንደሰረቀ ፣ የሃሰት መ ስካሪው ለምን ዋሽቶ እንዳስቀጣው ፣ ወንበዴው እንዴት አ ድፍጦ ማጅራት እንደመታ በግላጭ ሲያወጋ ፣ ቅምም አይ ለው ። አንተ እንዳልከው ፣ ወህኒ ቤትነቱ ሣይሆን የመከራ ትምሕርት ቤትነቱ ይበልጥ ይታየኝ ጀምሯል ። መከራ ቸው መከራዬ ፣ ጉዳቸው ጉዴ ፣ ጠረናቸው ጠረኔ መሆኑ እያ ደር ታወቀኝ ። ፀጉሬን ተላጭቼ መሃከላቸው ስገባ ፣ የሻማ አምጣ ብለው የደበደቡኝ ዕለት ፣ ምርር ያለ ቂም ይዤባቸው አደርኩ ። እያደር ግን የመንፈሴን እድፍ በዓይኖቻቸው መስታወት ውስጥ ሳስተውላት ምሬቴ ገርገብ ያለ መሰለኝ ። አብዬን ፣ የምሥራች ! ሴንጢ ብቻ ይጨብጡ የነበሩት እጆቼ ዛሬ ዝቅ ብለው አፈር መጫር ይማራሉ በልልኝ ። አንድ መ ጠነኛ የአትክልት መደብ ደልድዬ ጎመንና ሽንኩርት መኮት ኮት ይገፐለሁ በለው ። ግምባርክን አፈር ላይ ደፍተሀ ፣ ካፈር ታግለህ ፣ አፈር ቧጠህ የተከልከው ችግኝ ፣ ስር ሰደደ አልሰ ደደ ፣ አረም በላው አልበላው ፣ ፀሐይ ሸሸው ፣ ውሃ ጠማው ማለቱ ፣ አንተ እንዳልከው ሲሳይ መሆኑን ልማር ነው በለው ። . . . . . .

ጋሼ ፣ ምናልባት የምሬት ባርያ እንደሆንኩ እቀር ይሆናል ። ምናልባት እኔነቴን ከቶውንም ሳላውቀው በቅገርት ጨለማ እንደተሳከርኩ እቀር ይሆናል ። ግን ጋሼ ፣ እጄ አፈር መጫር መማሩን ፣ የእጄ ወዝ ከአፈር ተመሳቅሎ ፍሬ ማፍራቱን ማ



ወቁ ፣ አንተን ፣ በተለይም አብዬን ትንሽ ደስ ሳይለው አይቀ ርም በማለት ነው ይህን መጻፌ ። ማን ያውቃል ፣ ምናልባት ከዚህ ስወጣ ከአብዬ ጋር አባታችን እርስት ላይ ሄጄ ያፈርን ጣዕም በይበልጥ እማር ይሆናል ። . . . . ግን ፣ የዳግማዊ ምኒ ልክ ሆስፒታል ሐኪም በሴንጢ የወጋኋቸው ሰውዬ ሕይወ ት መትረፉ ያሰጋል የሚል መግለጫ ፈርሟል ስላሉ ፣ ከቶው ኑ ከዚህ አልወጣ ይሆናል ። አንተስ ይህን ሳትሰማ ቀርተህ ነው ? - ወይስ ይደነግጣል ብለህ ነው የደበቅኸኝ ? (ሞገስ ሲቃ ተናንቆት ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ይላል ፣ ወዲያው ማንበቡን ይቀጥላል -) በተረፈ በዓይነ ሥጋ ለመገናኘት ያብ ቃን ፣ አብዬን እግዚአብሔር ይማርህ በለው ። ምናልባት ከተፈታሁ አብረን እንሄድ ይሆናል ፣ ብሏል በልልኝ ። (ዘግየት ብሎ የሃዘን ሲቃ ባፈነው የፍሥሐ አንደበት -) ታዲ ያስ አብዬ ደስ አይልህም እንዴ ? . . . ያ-ያፈርን ጣዕም በመከራ ቤት ተማርኩ ነው እሚልህ ፣ . . . . . ወደ አባባ እርስት አብረን እንሄዳለን ነው የሚልህ ፣ . . . . (ወደ ዘርፉ ሄደት ብሎ -) አብዬ ። (ወደአልጋው ተጠግቶ -) አብዬ ። (ክንብንቡን በዝግታ ከፈት አርጎ ፣) አብዬ . . . አብዬ ! ! (በታላቅ ድንጋጤ ተነብዞ አፉን እንደከፈተ ይቀራል ። ወዲ ያው ወደግድግዳው የጭላንጭል ቀዳዳ ሄዶ ውታፉን ይከፍ ትና ሲቃ እያርበተበተው ከፍ ባለ ድምፅ -) አ-አቶ ተሊላ ፣ አ-አቶ ተሊላ ! ! እ-እ-እባክዎ ፣ አ-አጎቴ ከ-ካገር ቤት ለሕክ ምና መጥቶ አ-አርፏልና እድርተኞችዎ እ-እንዲያቃብሩኝ ያ ያስነግሩልኝ ። (የተሊላ ሳል ድቅቅ ብሎ ይሰማል ። ሞገስ ገድንጋጤ እንደተጨበጠ ወደራሱ አልጋ እየተርበተበተ

Scanned by CamScanner

ይሄድና ጥቁሩን ብርድልብስ ከአልጋው ላይ ገፍፎ የዘርፉን አስከሬን እየተንቀጠቀጠ ይጠቀልልበታል) እየተርበተበ ተና ጥርሶቹን ይያፋጩ ተመልሶ ሶፋው ግርጌ ኩርምት ብሎ ይታጠፍና ይንሰቀሰቃል ። ከደጅ ፡ የጎላ ሠፈር የእድርተኞች ለፋፊ ጡሩምባና ልፈፋ ሲሰማ መብራቱ በዝግታ ይጠፋል ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቤተ መጻሕፍት
A. A. UNIVERSITY
LIBRARIES